# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ

82ኛ ዓመት ቁጥር 192 መጋቢት 12 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር

DERBA CEMENT

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ


# የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን

## ለማበረታታትና ኮንትሮባንድን ለመቆጣጠር ቅንጅታዊ አሠራር ያስፈልጋል

ሞገስ ጸጋዬ



ፎቶ - ፀሐይ ንጉሤ

አዲስ አበባ፡- የሀገር ኢኮኖሚን ለማሳደግ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና ኮንትሮባንድን ለመቆጣጠር ቅንጅታዊ አሠራር እንሚያስፈልግ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ።

ሰባተኛው የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ሀገራዊ የቅንጅት መድረክ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አዘጋጅነት በትናንትናው ዕለት ሲካሄድ በመድረኩ ንግግር ያደረጉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን እንደገለጹት፤ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በመሳብ ኢኮኖሚውን ማነቃቃትና የኮንትሮባንድ እንቅስቃሴን ለመግታት የሚያስችል የቅንጅት ሥራ መሥራት ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ነው።

የምናመርተው ምርት በኮንትሮባንድ ወደ ጎረቤት ሀገራት እንዳይሄድ መቆጣጠርና የንግድ ሥርዓታችንን የማዘመን ሥራ በመሥራት የኑሮ ውድነቱን ማረጋጋት ይገባል ያሉት አቶ ደመቀ፤ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን ለማበረታታትና ኮንትሮባንድን ለመቆጣጠር የሁሉም አካላት ቅንጅታዊ አሠራር አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል።

ኢኮኖሚውን በሥርዓትና በቅንጅት መምራት ለሀገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ትልቅ ጥቅም እንዳለው ጠቁመውም፤ በ2003 ዓ.ም የቅንጅት መድረኩ ከተቋቋመ በኋላ ኢትዮጵያ በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ላይ ሰፊ ሥራ በመሥራትና የውጭ ኢንቨስተሮችን ከመሳብ አንጻር ትልቅ ሥራ መሥራቷን ተናግረዋል። በዚህም የሀገር ኢኮኖሚን ማነቃቃት መቻሉንና ሰፊ የኢንቨስትመንት አማራጮች መፈጠራቸውን አንስተዋል።

የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትን በስፋት


የውጭ ቀጥታ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



pepsi

የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን
ETHIOPIAN COMMUNICATIONS AUTHORITY

የሚሰጡ አገልግሎቶች
- ለቴሌኮም እና የፖስታ አገልግሎት አቅራቢዎች ፈቃድ መስጠት
- የቴሌኮም እና የፖስታ አገልግሎቶችን መቆጣጠር
- የፍሪኩዌንሲ እና የቴሌኮም ቁጥር ሀብቶችን ማስተዳደር
- የቴሌኮም መሳሪያዎችን የቴክኒክ ብቃት ማረጋገጥ
- የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎችን ቅሬታ መፍታትና መብት ማስጠበቅ
- የዘርፉን ፍትሃዊ ተወዳዳሪነት ማበረታታት
- ሁሉን አቀፍ የቴሌኮም አገልግሎት ተደራሽነትን ማረጋገጥ
- የኮሙኒኬሽን አገልግሎቶችን ታሪፍ መቆጣጠር

አድራሻ ከኤድናሞል ወረድ ብሎ ሮቤል ፕላዛ ህንፃ
+251-11-692-80-42
9991
contact@eca.et
https://www.eca.et

ጥራት ያለው የኮሙኒኬሽን አገልግሎት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርብ እንጥራለን!


# ለ250 ሺህ ምሩቃን

## የመውጫ ፈተና ለመስጠት ዝግጅት እየተደረገ ነው

ፋንታነሽ ክንዴ

አዲስ አበባ፡- በተያዘው ዓመት 250 ሺህ ለሚጠጉ የመጀመሪያ ዲግሪ ተመራቂዎች የዩኒቨርሲቲ መውጫ ፈተና ለመስጠት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ።

በትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ጥራትና ብቃት ማሻሻያ ዴስክ ኃላፊ አቶ ሰይድ መሐመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሀገር ደረጃ አንገብጋቢ ችግር ሆኖ እየተነሳ ያለውን የትምህርት ጥራት መጓደል ችግር ለመቅረፍ ከሚወሰዱ ርምጃዎች አንዱ የዩኒቨርሲቲ መውጫ ፈተና መስጠት ነው። በመሆኑም በተያዘው ዓመትም 250 ሺህ ለሚጠጉ ተማሪዎች የመውጫ ፈተና ይሰጣል።



ከዚህ ቀደም በጤናና በሕግ የትምህርት መስኮች ለሚመረቁ ተማሪዎች ብቻ የመውጫ ፈተና ሲሰጥ መቆየቱን አስታውሰው፤ በያዝነው ዓመት ከመጭው ሐምሌ ወር ጀምሮ ከየትኛውም ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በመጀመሪያ ዲግሪ ለሚመረቁ ተማሪዎች የመውጫ ፈተና ለመስጠት ዝግጅት በመጠናቀቅ ላይ መሆኑን ጠቁመዋል።


ለ250 ሺህ ምሩቃን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


# ግብርና ሚኒስቴር

## በድርቅ ለተጎዱ ክልሎች ከ394 ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ አደረገ

ዳግማዊት አበበ

አዲስ አበባ፡- ድርቅ በተከሰተባቸው ሶስት ክልሎች ለአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ የሚሆን የ 394 ሚሊዮን ብር ድጋፍ ማድረጉን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

በግብርና ሚኒስቴር የእንስሣትና ዓሳ ሀብት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ፍቅሩ ረጋሳ (ዶክተር) እንደገለጹት፤ ድጋፉ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ በኦሮሚያና በሶማሌ ክልሎች በተከሰተው ድርቅ ምክንያት ለተጎዱ አካባቢዎች የሚውል ነው።

ግብርና ሚኒስቴር ከዓለም ባንክና ከአውሮፓ ኅብረት ያገኘውን ለአስቸኳይ ጊዜ ርዳታ የሚሆን 394 ሚሊዮን


ግብርና ሚኒስቴር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



AMG STEEL FACTORY
ኤ.ኤም.ጂ ብረታ ብረት ፋብሪካ
Our Products
GI-Coil Color Coil Tiles
Ega Sky Tiles Corrugated Sheet Curving Ridge Sky Ridge V-Gutter Accessories
Tel: 0920 65 65 65 / 0940 60 60 60 / 0940 80 80 80/ 0940 81 81 81 / 0940 90 90 90 / 0979 06 06 06

AfriSky PLC ETHIOPIA
Our Products
Billet RHS Wire Rod Re-bar CZU H-BEAM Nail Streel Structure Tanker
Akaki, Gelan
0920 65 65 65 / 0940 60 60 60 / 0940 80 80 80
0940 81 81 81 / 0940 90 90 90 / 0979 06 06 06

# በወረዳው ከሁለት ነጥብ አንድ ሚሊዮን በላይ ችግኞች ስተከላ ተዘጋጅተዋል

**ዳግማዊት ግርማ**

ቦሪቻ (ሲዳማ)፡- በሲዳማ ክልል በሚገኘው ቦሪቻ ወረዳ አረንጓዴ አሻራን ለመተግበር ከሁለት ነጥብ አንድ ሚሊዮን በላይ ችግኝ ማዘጋጀቱን የወረዳው ግብርናና እርሻ ልማት ጽህፈት ቤት አስታወቀ።

ጽህፈት ቤቱ በኅብረተሰብ አቀፍ የተፋሰስ ልማት ንቅናቄው 35 ሚሊዮን ብር የሚተመን አገልግሎት በነጻ ለማሰራት ማቀዱንም ገልጿል። የጽህፈት ቤቱ ኃላፊ አቶ ራህመቶ አዳሞ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በሚቀጥለው ክረምት ወቅት የሚተገበረው የአረንጓዴ አሻራ ፕሮግራምን ለማሳካት ከሶስት ሚሊዮን በላይ ችግኞችን ለማዘጋጀት ታቅዶ እስከአሁን ሁለት ነጥብ አንድ ሚሊዮን በላይ ችግኞችን ማዘጋጀት ተችሏል። አፈጻጸሙም የእቅዱን ሰማንያ አምስት በመቶ ነው።

የቦሪቻ ወረዳ ተደጋጋሚ በሆነ የውሃ እጥረት ምክንያት የድርቅ ተጋላጭ እንደነበር ያወሱት አቶ ራህመቶ፤ በህብረተሰቡና በመንግሥት በተደረገው ያላሰለሰ ጥረት አሁን አየር ንብረቱ ወደ መሻሻል መጥቷል ብለዋል።

45ሺህ የሚጠጉ ሰዎችን ተሳታፊ ባደረገው ኅብረተሰብ አቀፍ የተፋሰስ ልማት ስራ ንቅናቄው ከተጀመረበት ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ ከ8ሺህ በላይ ሄክታር መሬት ማልማት መቻሉን ተናግረው፤ በዘንድሮው ንቅናቄ ብቻም አራት ሺህ 450 ሄክታር እንደሚለማም ነው ያስረዱት።

ወረዳው የድርቅ ተጋላጭ በመሆኑ መሬቱ ከፍተኛ ጉዳት ይደርስበት እንደነበር ያወሱት አቶ ራህመቶ፤ ዘንድሮ እየተካሄደ ባለው የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት ከምንጊዜውም የተሻለ ስራ ለመስራት መንግሥትና ኅብረተሰቡ እየተረባረቡ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ባሳለፍነው ዓመት በተሰራው የተፋሰስ ልማት 29 ነጥብ 5 ሚሊዮን ብር የሚገመት የነጻ አገልግሎት በኅብረተሰቡ መሰጠቱን ያወሱት ኃላፊው፤ ባለፈው ዓመት ከነበረው መልካም ተሞክሮ በመውሰድ በተያዘው ዓመትም 34 ነጥብ 9 ሚሊዮን ብር በላይ ለማዳን መታቀዱንም አክለው ገልጸዋል።

በወረዳው ላለፉት አስራ ሁለት ዓመታት በተከናወነው የተፋሰስ ልማት ስራ የተጎዱ አካባቢዎችን በተለያዩ እፅዋት መሸፈን በመጀመራቸው፤ ለሰብል ልማት ምቹ ሁኔታ መፍጠሩንና ለአፈር መሸርሸር ተጋላጭነቱ እየቀነሰ መምጣቱን አቶ ራህመቶ ተናግረዋል።

በተሰሩ የተፋሰስ ልማት እንቅስቃሴዎች በአፈር መሸርሸር ምክንያት የሚፈናቀሉ አርሶአደሮች ቁጥር መቀነሱን፣ ከሰባ ስምንት በመቶ በላይ ቆላማ የነበረው አካባቢ ወደ ደጋማነት መቀየሩ እንዲሁም የአርሶ አደሮች ምርትና ምርታማነት በብዙ መጨመሩን አቶ ራህመቶ አብራርተዋል።



# «በምግባችን ከደጃችን» መርሀ ግብር ከ237 ሺህ በላይ አባወራዎችና እማወራዎች ተጠቃሚ ሆነዋል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ እየተካሄደ ባለው “ምግባችን ከደጃችን” መርሀ ግብር ከ237 ሺህ በላይ አባወራዎችንና እማወራዎችን ተጠቃሚ ማድረጉን የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን ገልጿል።

የከተማ ግብርና ልማት ኮሚሽን የኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክተር አቶ ወንድወሰን አካሌ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአዲስ አበባ ከተማ የፍጆታ ምርትን ለከተማው ሕዝብ ለማቅረብ በተለያዩ አካባቢዎች ያሉ የከተማዋ ነዋሪዎች በከተማ ግብርና ላይ ተሰማርተዋል።

የምግብ ፍጆታን ለመሸፈን “ምግባችን ከደጃችን” በሚል መርሃግብር የጓሮ እና የማሳ አትክልቶችን በመትከልና በመንከባከብ ከሌማት ትሩፋት ጋር በማቀናጀት በርካታ ስራዎች እየተሰራ ነው። እንደ አቶ ወንድወሰን ገለጻ፤ በመርሃግብሩ 286ሺ አባወራዎችና እማወራዎች ተጠቃሚ ለማድረግ ታቅዶ እስካሁን ከ237 ሺ በላይ አባወራዎች ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን አብራርተዋል።

በምግባችን ከደጃችን ፕሮግራም በአዲስ አበባ በ11ዱም ክፍለ ከተሞች ባሉ ሁሉም ወረዳዎች ላይ በማሳና በጓሮ አትክልት፣ በእንስሳት ልማት እና በዶሮ ርባታ በቤተሰብ ፍጆታ ልክ የከተማው ነዋሪ ተጠቃሚ ለማድረግ እየተሰራ ነው ።

በዶሮ ርባታ በቤተሰብ ደረጃ ቢያንስ 5 ዶሮዎችን እንዲያረቡና የቤተሰቡን የእንቁላል ፍጆታ እንዲሸፍኑ እየተሰራ ይገኛል። ለዚህም ሥልጠናዎችንና ክትባቶችን በመስጠት እና የተመረጡ ዝርያዎችን በማቅረብ ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችላቸውን ድጋፍ እየተደረገ ነው። የሥልጠና ሂደቱም ሁሉን ያካተተ እንዲሆን በሁሉም ክፍለ ከተሞች ባሉ አርሶ አደርና ከተማ ግብርና ልማት ጽህፈት ቤት ኃላፊዎችና ባለሙያዎችን በማሰልጠን ለከተማው ነዋሪዎች ሥልጠና እንዲሰጡ ተደርጓል።

ከዚህ በተጨማሪም ከ40 በላይ የሚሆኑ የማዕከል ባለሙያዎችን በ11ዱም ክፍለ ከተሞች ድጋፍና ክትትል እንዲያደርጉ ተመድበው እየሰሩ ነው። አርሶ አደሮች የውሃ አቅርቦት ችግር እንዳያጋጥማቸው ውሃን በቀላሉ ማግኘት የሚያስችላቸውን የውሃ ቦቲ ተሽከርካሪ መከራየት እንዲችሉም ተደርጓል።

200 የውሃ መሳቢያ ሞተሮች ለአርሶ አደሮች ተሰራጭተዋል። ነዋሪዎችን በማሳና የጓሮ አትክልት ተጠቃሚ የማድረግ ስራ በ2014 ዓ.ም ተጀምሮ እስከ አሁን ተጠናክሮ ቀጥሏል ያሉት አቶ ወንድወሰን፤ በእንስሳት እርባታ ረገድም ጅምር ስራዎች ተጠናክረው የሚቀጥሉ ይሆናል ብለዋል።



# በመዲናዋ ከ80 ሺህ ኪሎ ግራም በላይ የአገልግሎት ዘመን ያለፈባቸው መድኃኒቶች ተወገዱ

## - ለሥራው 103 ሚሊዮን ብር ወጪ ተደርጓል

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ ባለፉት ስምንት ወራት ከ78 የግል መድኃኒት ቸርቻሪ ድርጅቶች እና ጤና ተቋማት ከ80 ሺህ ኪሎ ግራም በላይ የአገልግሎት ዘመን ያለፈባቸው መድኃኒቶች መወገዳቸውን የአዲስ አበባ ምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባሥልጣን ገለጸ።

የአዲስ አበባ ምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባሥልጣን፣ የጤና ተቋም ብቃት ማረጋገጥና ቁጥጥር ዳይሬክተር ወይዘሮ በድሪያ ሁሴን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት ስምንት ወራት በመዲናዋ በሚገኙ በ78 የግል የመድኃኒት ቸርቻሪ ድርጅቶችና የጤና ተቋማት መደበኛና ድንገተኛ ፍተሻ ተደርጓል። በዚህም 80 ሺህ 620 ኪሎ ግራም የአገልግሎት ዘመን ያለፈባቸው መድኃኒቶች ተገኝተው ተወግደዋል።



ከዚህ በፊት የነበረው የመድኃኒቶች አወጋገድ ሂደት መሬት ውስጥ ስለሚቀበር የአፈርና የውሃን ብክለት የሚያስከትል ነበር ያሉት ዳይሬክተሯ፤ የአፈርና የውሃን ብክለትን ለመከላከል መድኃኒቶችን በማሽን ውስጥ በከፍተኛ ሙቀት እንዲቀልጥ በማድረግ የማስወገድ ሥራ ተጀምሯል ብለዋል። ይህንን ለማድረግም 103 ሚሊዮን ብር ወጪ ተደርጓል።

የመንግሥትና የግል መድኃኒት ቸርቻሪ ድርጅቶች የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶችን የማስወገድና የቅድመ ማስወገድ ሥራ እንዲሠሩ ክትትልና ቁጥጥር እያደረገ ይገኛል ያሉት ወይዘሮ በድሪያ፤ የአገልግሎት ዘመን ያለፈባቸው መድኃኒቶችን ተከታትሎ ለማስወገድ በዓመት ሁለት ጊዜ በመድኃኒት ቸርቻሪ ድርጅቶችና በጤና ተቋማት ላይ መደበኛ ፍተሻ እንደሚደረግ ገልጸዋል። ያለውን ችግር ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚደረገው መደበኛ ፍተሻ በቂ ባለመሆኑ ያልተጠበቀ ፍተሻም ይደረጋል ነው ያሉት።

በመድኃኒት ቸርቻሪ ድርጅቶችና በጤና ተቋማት ላይ በሚደረግ ያልተጠበቀና ድንገተኛ ፍተሻ የአገልግሎት ዘመን ያለፈባቸውና በመንግሥት የጤና ተቋማት ብቻ ሊገኙ የሚገቡ መድኃኒቶች በህገወጥ መንገድ በግል የመድኃኒት ቸርቻሪ ድርጅቶች ገብተው እንደሚገኙ አብራርተውም፤ በዓመት ሁለት ጊዜ ከሚደረገው መደበኛ ፍተሻ ይልቅ በድንገት የሚደረገው ፍተሻ ውጤታማ ነው ብለዋል።

የአገልግሎት ዘመን ያለፈባቸውን መድኃኒቶች ሳያስወግዱ በሚገኙ የመድኃኒት ቸርቻሪ ድርጅቶችና የጤና ተቋማት ላይ ከሦስት ወር እስከ አንድ ዓመት የእገዳና አስተዳደራዊ እርምጃ እንደሚወሰድባቸውም አክለው ገልጸዋል።

እንደ ወይዘሮ በድሪያ ገለፃ፤ የመድኃኒት አቅርቦት ወደ ፊት እጥረት ሊገጥም ይችላል በሚል ስጋትና ከፍተኛ በሆነ ዋጋ ለመሸጥ በሚደረግ ከፍተኛ የሆነ ክምችት መድኃኒቶች ተጠቃሚ ላይ ሳይደርሱ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያልፋል። እነዚህ መድኃኒቶች ተመልሰው ለግልግሎት እንዳይውሉ ባለሥልጣን መስሪያ ቤቱ ባለሙያዎችን መድቦ እስከ መጨረሻ መወገዳቸውን የማረጋገጥ ሥራ ይሠራል።

የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው መድሃኒቶችን የያዙ የጤና ተቋማት መድኃኒቶችን ለማስወገድ፤ የማስወገጃ ማሽን ካላቸው የጤና ተቋማት ጋር በቅንጅት እንዲሰሩና ማህበረሰቡ መድኃኒቶችን ሲገዛ ከባለሙያ በቂ የሆነ ግንዛቤ ይዞ በመሄድ ጤናውን ሊጠብቅ ይገባል ሲሉ አሳስበዋል።



አቶ ባዩ አብሃይ

# በጎንደር ከተማ የተከሰተውን የኑሮ ውድነት ለማረጋጋት እየተሰራ ነው

**ቤዛ እሸቱ**

ጎንደር፡- በሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ተጽዕኖዎች ምክንያት በጎንደር ከተማ የተከሰተውን የኑሮ ውድነት ለማረጋጋት እየተሰራ መሆኑ ተገለጸ።

የጎንደር ከተማ አስተዳደር ምክትል ከንቲባ አቶ ባዩ አብሃይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ በጎንደር ከተማ የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት በትኩረት እየተሰራ ነው። በሀገር አቀፍም ሆነ ዓለም አቀፍ ተጽዕኖዎች ምክንያት በተፈጠረው የኑሮ ውድነት ጎንደር ከተማም ተጠቂ ነች። የኑሮ ውድነቱን ለማረጋጋት ወደ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶች ላይ ቁጥጥርን ማጠናከር አንዱ ሲሆን፤ በሌላ በኩል የሸማች ማህበራትን አቅም ለማጠናከር ከተማ አስተዳደሩ እየሰራ ነው።

እንደ ምክትል ከንቲባው ገለጻ፤ ከተማ አስተዳደሩ የሸማች ማኀበራት መሰረታዊ ምርቶችንና የግብርና ምርቶችን ለሕብረተሰቡ በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ እንዲችሉ 20 ሚሊዮን ብር መድቧል። በዚህ በመታገዝ ማህበራቱ ለመንግሥት ሠራተኛው ጤፍና ሌሎች ሸቀጣሸቀጦችን በተመጣጣኝ ዋጋ እያከፋፈሉ ይገኛሉ። በቀጣይም የከተማ አስተዳደሩ ዳቦን በተመጣጣኝ ዋጋ አምርቶ ማቅረብ የሚያስችል ፕሮጀክት ጀምሯል። ለዚህም የመሸጫ ቦታዎችን ዝግጅትና ሌሎች የቅድመ ዝግጅት ሥራዎችን እያከናወነ ነው።

ዳቦን ለከተማው ነዋሪ በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ ከተማ አስተዳደሩ ለስንዴ ግዢ በጀት መመደቡን የገለጹት አቶ ባዩ አብሃይ፤ ከተለያዩ አካባቢዎች ስንዴን በማምጣት ዱቄትን በተመጣጣኝ ዋጋ ለኅብረተሰቡ ለማቅረብ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየሠራን እንገኛለን ብለዋል። የከተማ አመራሩ የኑሮ ውድነትን ለማርገብ የሚያስችል ሥራ ከመስራት ጎን ለጎን ገበያን ሊያረጋጉ የሚችሉ ሥራዎችን ትኩረት ሰጥቶና በጀት መድቦ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል ነው ያሉት።

የጎንደር ከተማ ምግብ ዋስትና ጽህፈት ቤት ኃላፊ ወይዘሮ ሀዲያ መሀመድ በበኩላቸው፤ በፕሮጀክቱ አማካኝነት የኑሮ ውድነቱን ለመግታት የከተማ ግብር ስራ እየተከናወነ እንደሚገኝ ገልጸዋል። የምግብ ዋስትናና ሴፍቲኔት በጎንደር ከተማ በታህሳስ 2014 ዓ.ም የተጀመረ ሲሆን፤ ከአምስት ሺ በላይ ዜጎች ተጠቃሚ ሆነዋል። የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች ለቤት ውስጥ ፍጆታ የሚያውሉትን አትክልት በውድ ገዝተው ከሚጠቀሙ ይልቅ የጓሮ አትክልቶችን እንዲያለሙ እየተደረገ እንደሚገኝ ተናግረዋል።

# «በሲዳማ ክልል ያለውን የመልማት አቅም አሟጦ በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በትኩረት እየተሠራ ነው»

- አቶ ደስታ ሌዳሞ
  የሲዳማ ክልል ርዕሰ መስተዳድር

**አምሳሉ ፈለቀ**

ሐዋሳ፡- በክልሉ በሁለንተናዊ ዘርፍ ላይ ያለውን የመልማት አቅም አሟጦ በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የተጀመሩ ሥራዎች አበረታች መሆናቸውን የሲዳማ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ደስታ ሌዳሞ ገለጹ።

ርዕሰ መስተዳድሩ ይህንን ያሉት ትናንት በሐዋሳ ከተማ መካሄድ በጀመረው የክልሉ ምክር ቤት 6ኛ ዙር 2ኛ የሥራ ዘመን 4ኛ መደበኛ ጉባዔ ላይ ነው።

የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ ደስታ ሌዳሞ እንዳሉት፤ በክልሉ የኅብረተሰቡን ምርትና ምርታማነትን ለማረጋገጥ በምግብ እህል ራስን ከመቻል አልፎ ለገበያ የሚቀርብ ትርፍ ምርት ለማምረት ትኩረት ተሰጥቷል። በዚህም ምርታማነትን በማሳደግ የኢኮኖሚ ዕድገትና ብልጽግናን ለማረጋገጥ ባለድርሻ አካላትንና ኅብረተሰቡን በማሳተፍ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

በኢኮኖሚው ዘርፍ ውጤት ማስመዝገብ የሚቻልባቸው ዘርፎች ላይ ትኩረት የተደረገ ሲሆን፤ በተለይም የቡና፣ የአዝዕርት እህል፣ ለተለያዩ የፋብሪካ ግብዓትነት የሚውሉ እንዲሁም በእንስሳት ምርትና ምርታማነትን የሚጨምሩ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ።

በተያዘው የበጀት ዓመት ባለፉት ሰባት ወራት በተለይ የበጋ መስኖ ስንዴን በመጀመሪያው ዙር 54 ሺህ 131 ሄክታር መሬት ላይ ለማልማት ታቅዶ እስካሁን ድረስ 51 ሺህ 328 ሄክታር መሬት ለማልማት ተችሏል።

ለቡና፣ ቅመማቅም፣ በእንሰት ልማት እንዲሁም ለተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆኑ የፍራፍሬ ምርቶች ላይ ትኩረት በመስጠት በየአካባቢው በርካታ አርሶ አደሮች ተቀናጅተው እንዲያለሙ እየተደረገ መሆኑም ተገልጿል።



የክልሉን የውስጥ ገቢ አቅም በማሳደግ የኅብረተሰቡን የመልማት ፍላጎት ለማሟላት የሚያስችል ገቢን ለማመንጨት በበጀት ዓመቱ 10 ቢሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ የታቀደ ሲሆን፤ በመጀመሪያ ግማሽ ዓመት ለመሰብሰብ ከታቀደው 6.2 ቢሊዮን ብር 4.3 ቢሊዮን በላይ ገቢ ተሰብስቧል። በቀሩት ጊዜያትም የዓመቱን ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑም ተጠቁሟል።

የኅብረተሰቡ ዋነኛ ጥያቄ ከሆኑት የንጹህ መጠጥ ውሃ ተደራሽነት፣ የመንገድ፣ የመብራትና ሌሎችም መሠረተ ልማቶችን ተገቢው ትኩረት ተሰጥቷቸው የተሠሩ ሲሆን፤ ከዚህም ቀደም ተጀምረው የተጓተቱ ፕሮጀክቶች እንዲጠናቀቁና አዳዲስ ፕሮጀክቶችም በአጭር ጊዜ ውስጥ ተጠናቅቀው ለኅብረተሰቡ አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ ተችሏል።

ክልሉን በኢኮኖሚ፣ ብሎም የቤተሰብ ብልጽግናን በማረጋገጥ ረገድ ተወዳዳሪ እንዲሆን ለማስቻል ከቡና ልማት ቀጥሎ የእንስሳት ሀብቱ ዋነኛ የዕድገት ምንጭ መሆኑን የጠቆሙት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ የእንስሳቱን ዝርያ በማሻሻል በከተማም ሆነ በገጠር የእንስሳት ርባታን በማስፋፋት፣ ምርትና ምርታማነትን የማሳደግና በዘርፉም ተጠቃሚነትን ለማሳደግ ትኩረት መሰጠቱን አስታውቀዋል።

በበጀት ዓመቱ በከተማና በገጠር አካባቢዎች በአጠቃላይ 51 ሺህ 614 ለሚሆኑ ሥራ ፈላጊ ወጣቶች በተለያዩ ዘርፎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዶ ባለፉት ሰባት ወራት 30 ሺህ 264 ወጣቶች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል። ለወጣቶች መነሻ ካፒታል የብድር አቅርቦት 62.3 ሚሊዮን ብር ተመቻችቶላቸዋል ተብሏል። የተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ከማስፋፋት አኳያም በክልሉ መንግሥት እና ባለድርሻ አካላት የተሠሩ ሥራዎች አበረታች እንደሆኑ ተጠቁሟል።

በተለይም የዘንድሮውን የ12ኛ ክፍል ውጤትን መነሻ በማድረግም “የሲዳማ የትምህርት ትንሣዔ” በሚል የትምህርት ሥራን በዋናነት የሚከታተልና በቀጣይም የተማሪዎችን ውጤትና ሥነምግባር ለማሻሻል የሚያስችል ግብረ ኃይል ተቋቁሞ እየተሠራ እንደሆነም ነው ርዕሰ መስተዳድሩ የጠቆሙት።

ኅብረተሰቡን የሚያማርሩ ብልሹ አሠራሮችንና ሙስናን በመታገል መልካም አስተዳደርን ለማስፈንም በዋናነት ኅብረተሰቡን በማሳተፍ በብልሹ አሠራር እጃቸው ያለባቸውን አካላትም ተጠያቂነት የማድረግና የሕግ የበላይነት እንዲከበር እየተሠራ ስለመሆኑም ገልጸዋል።

# የነዳጅ ፍጆታን ለመቀነስ የብዙኃን ትራንስፖርት አገልግሎት መስፋፋት አለበት

**መክሊት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ እያደገ የመጣውን የነዳጅ ፍላጎት ለማረጋጋት መንግሥት የብዙኃን ትራንስፖርት አገልግሎትን ለማስፋፋት እያደረገ ያለውን ጥረት አጠናክሮ መቀጠል አለበት ሲሉ ምሁራን ተናገሩ።

ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ቆይታ ያደረጉት የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ዛፉ እየሱስወርቅ፤ የብዙኃን ትራንስፖርት አገልግሎትን በማስፋፋት የግል ተሽከርካሪዎችን ቁጥር በመቀነስ የነዳጅ ፍጆታችንን ማረጋጋት እንችላለን ሲሉ ተናግረዋል።

እንደ አቶ ዛፉ ገለጻ፤ አዲስ አበባ ከፍተኛ የተሽከርካሪዎች ፍሰት ያለባት ከተማ ነች። በመሆኑም የብዙኃን ትራንስፖርት ላይ ትኩረት መደረጉ ለነዳጅ የሚወጣውን የውጭ ምንዛሬ ከመቀነሱ ባሻገር በመንገድ መዘጋጋት የሚቃጠለው ነዳጅ ለመቀነስም ይረዳል።

የብዙኃን ትራንስፖርት አገልግሎቶችን ተደራሽነት በማስፋፋት የነዳጅ ፍጆታን መቆጠብ ይቻላል ያሉት አቶ ዛፉ፤ በሌላ በኩል በአንድ የግለሰብ መኪና አንድ ተጓዥ ብቻ ይዞ መጓዝ አይችልም የሚል ሕግን በመቅረጽ ለነዳጅ የሚወጣውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ መቀነስ እንደሚቻል አብራርተዋል።

የፋይናንስ እና ኢኮኖሚ አማካሪ የሆኑት አቶ አብድልቃድር ኑረዲን በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ ላይ ያለው የነዳጅ ዋጋ ዓለምአቀፋዊ በሆኑ ምክንያቶች የጨመረ መሆኑን አስረድተው የሀገሪቱን የነዳጅ ፍጆታ ለመቀነስ አማራጭ የብዙኃን ትራንስፖርቶችን ማስፋት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል።

ዋነኛው የዓለምአቀፍ የነዳጅ ዋጋ መጨመር ከዩክሬን እና ከሩሲያ ጦርነት ጋር የተያያዘ እንደሆነ



አቶ አብድልቃድር ኑረዲን



አቶ ዛፉ እየሱስወርቅ

አብራርተው፤ የነዳጅ ጭማሪ በመኖሩ በአንዳንድ የጎረቤት ሀገራት ጭምር ነዳጅ በኮታ እንዲሆን ተደርጓል ነው ያሉት።

ኢትዮጵያ ላይ የነዳጅ ድጎማ መኖሩ ዝቅተኛ የገቢ ምንጭ ያለውን የማኅበረሰብ ክፍል ሊረዳ እንደሚችል ያብራሩት አቶ አብድልቃድር፤ ነገር ግን መንግሥት ድጎማ ከማድረጉ ጎን ለጎን ቁጥጥሮችም አጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አመላክተዋል። የተደረገው ድጎማ በትክክል ለተገቢው ዓላማ እንዲውል እና ኅብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ መንግሥት ቁጥጥሩን ማጠናከር አለበት ሲሉም አክለዋል።

አቶ አብድልቃድር እንዳሉት፤ በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ባቡሮችን መዳረሻቸውን ማስፋት እና የኤሌክትሪክ መኪናዎችን ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት የነዳጅ ፎጆታን ለመቀነስ የሚደረገው እንቅስቃሴ መቀጠል አለበት። የዲጂታል አገልግሎት ሲስተሞችን በማስፋት የኅብረተሰቡን እንቅስቃሴ ለመቀነስ ቢሰራም ጥሩ ውጤት ይገኝበታል ብለዋል።

# «በከተማዋ ያጋጠመው የኤሌክትሪክ መቆራረጥ ችግር ወደ ነበረበት እየተመለሰ ነው»

*- ዶክተር ገበየሁ ሊካሳ*
*የአዲስ አበባ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈጻሚ*

# «በፈረቃ የውሃ አቅርቦት ላይ የተፈጠረው ችግርም እየተፈታ ይሄዳል»

*- አቶ ፍቃዱ ዘለቀ*
*የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ምክትል ሥራ አስኪያጅ*

**ጌትነት ምህረቴ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በአዲስ አበባ ከተማ ባለፉት ሁለት ሳምንታት ያጋጠመው የኤሌክትሪክ መቆራረጥ ችግር ወደ ነበረበት መመለሱን የአዲስ አበባ ኤሌክትሪክ አገልግሎት አስታወቀ። በኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ ምክንያት የነበረው የፈረቃ ሥርጭት መዛባት እየተስተካከለ መሆኑን የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ገልጿል።

የአዲስ አበባ ኤሌክትሪክ አገልግሎትና የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ትናንት በጋራ በሰጡት መግለጫ የአዲስ አበባ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ዋና ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር ገበየሁ ሊካሳ እንዳሉት፤ በከተማዋ ባጋጠመው ከባድ የአየር ሁኔታ፣ በግንባታ ፕሮጀክቶች፣ በኤሌክትሪክ መስመሮች ስርቆት፣ ባረጁ መስመሮችና የማከፋፈያ ጣቢያዎች ጥገና ምክንያት ባለፉት ሁለት ሳምንታት በከተማዋ በተለያዩ አካባቢዎች የኤሌክትሪክ ኃይል የመቆራረጥ ችግር ሲያጋጥም ቆይቷል። ችግሩን ለመፍታት አገልግሎቱ ባደረገው ፈጣን ጥገናዎችና ስራዎች አገልግሎቱን ቀድሞ ወደ ነበረበት መመለስ ተችሏል።

በተለይ በከተማዋ በወቅቱ የአየር ሁኔታን ተከትሎ ከባድ ዝናብና ንፋስ በመከሰቱ በኤሌክትሪክ ኃይል መስመሮች ላይ ችግር ፈጥሯል ያሉት ዶክተር ገበየሁ፤ ከባድ ዝናብ በከተማዋ ካሉት 137 መጋቢ መስመሮች ውስጥ በ50ዎቹ ላይ ጉዳት ማድረሱን ተናግረዋል።

በከተማው ውስጥ የሚካሄዱ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች ተግባራት በመስመሮች ላይ ጉዳት አድርሰዋል። በቤላ፣ በንፋስ ስልክና በኮልፌ በሚገኙ ማከፋፈያ ጣቢያዎች ላይ የተደረገው የጥገና ስራ ለኤሌክትሪክ መቆራረጥ መንስኤ መሆናቸውን አብነት ጠቅሰዋል።

ችግሩ ከተከሰተበት ጊዜ አንስቶ በተደረጉ የጥገናና ሌሎች ተጨማሪ ሥራዎችም ችግሩን መፍታት መቻሉን ነው ያስረዱት።

በዘላቂነት የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት ላይ የመቆራረጥ ችግር እንዳይፈጠርም አገልግሎቱ መስመሮችንና ማከፋፈያ ጣቢያዎችን የመጠገንና







የግንባታ ስራዎችን እያከናወነ መሆኑን ኃላፊው አመልክተዋል።

አራት ምዕራፎች ያሉት የማከፋፈያ ጣቢያዎችና የመስመሮች መልሶ ግንባታ እየተካሄደ መሆኑን ጠቁመው፤ በ 10 ቢሊዮን ብር የተካሄዱት የመጀመሪያውና ሁለተኛው ምዕራፍ ግንባታዎች በ2013 እና 2014 ዓ.ም መጠናቀቃቸውን አስታውሰዋል።

ሶስተኛ ምዕራፍም መልሶ ግንባታም በአብዛኛው የከተማው ክፍሎች እየተካሄደ መሆኑንና በ2016 ዓ.ም አጋማሽ ላይ እንደሚጠናቀቅ ጠቁመው፤ የአራተኛው ምዕራፍ የመልሶ ግንባታ ስራም ደግሞ በዚህ ዓመት ተጀምሯል፤ በ2017ዓ.ም የሚጠናቀቅ ይሆናል። ባለሥልጣኑ ለከተማዋ ነዋሪዎች የሚሰጠውን አገልግሎት ለማዘመንም ብዙ ስራዎችን እየሰራ እንደሚገኝም ነው የተናገሩት፡

እንደ ስራ አስፈጻሚው ገለጻ፤ ባለፉት ሁለት ሳምታት ጊዜያዊ የኃይል መቆራረጥ ችግር ተከስቷል። ይህም የደንበኞቻችን አስተማማኝ የኃይል አቅርቦት አስተጓጉሏል። በኤሌክትሪክ ኃይል ላይ ተመስርተው አገልግሎታቸውን ለሕዝብ በሚያቀርቡ ተቋማት ላይም አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥሯል። አገልግሎቱ በኃይል መቆራረጡ ምክንያት በደንበኞቹ ላይ ለተፈጠረው ችግር ይቅርታ ይጠይቃል ብለዋል።

የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ምክትል ሥራ አስኪያጅ አቶ ፍቃዱ ዘለቀ በበኩላቸው፤ ባለፉት ሦስት ሳምንታት ከወትሮው በተለየ የውሃ አቅርቦት መቆራረጥ ማጋጠሙን ገልጸው፤ በኃይል መቆራረጥ ምክንያት በአቃቂ ፤በንፋስ ስልክ፣ በቂርቆስና ኮልፌ ክፍለ ከተሞች በሙሉና በከፊል፤ በምዕራብና በምስራቅ አዲስ አበባ በተወሰኑ ቦታዎች የነበረው የውሃ አቅርቦት የፈረቃ ሥርጭት ላይ መዛባት መፈጠሩን አስታውሰዋል።

የኤሌክትሪክ ኃይሉ እየተስተካከለ መምጣቱን ተከትሎ የፈረቃ መዛባቱም ወደ ነበረበት እንደሚሄድ ተናግረዋል።

በከተማዋ በቀን አንድ ነጥብ ሁለት ሜትር ኩብ ውሃ ፍላጎት ቢኖርም ባለሥልጣኑ በቀን እስከ 725ሺህ ሜትር ኪዩብ ውሃ እያመረተ እንደሚገኝና አሁንም የአቅርቦት እና ፍላጎት አለመጣጣም መኖሩን ገልጸዋል።

ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የተለያዩ ፕሮጀክቶች ተቀርፀው ወደ ሥራ መገባቱንም አቶ ፍቃዱ አመልክተዋል።



ፍቅሩ ረጋሳ (ዶክተር)

## ግብርና ሚኒስቴር ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ብር ለሶስቱ ክልሎች ድጋፍ አድርጓል ያሉት ዶክተር ፍቅሩ፤ በክልል ደረጃም ለኦሮሚያ ክልል 170 ሚሊዮን ብር፣ ለሶማሌ ክልል 160 ሚሊዮን ብር፣ እንዲሁም ለደቡብ ክልል 64 ሚሊዮን ብር ድጋፍ መደረጉን ገልጸዋል።

ድርቅ በተከሰተባቸው ስፍራዎች በርካታ እንስሳቶች እንደተጎዱ እና ኅብረተሰቡ ችግር ውስጥ መውደቁን የጠቆሙት ዶክተር ፍቅሩ፤ የገንዘብ ድጋፉ በተቋቋመው የባለሙያዎች ቡድን አማካኝነት ድርቁ የተከሰተባቸው አካባቢዎችን በመከታተልና የቀረበውን ሪፖርት መሰረት በማድረግ ለተለያዩ ሥራዎች እንደሚውል ተናግረዋል።

ድጋፉ ድርቁ በተከሰተባቸው አካባቢዎች ላይ የእንስሳት መኖ በሚያስፈልግበት ቦታዎች ላይ መኖ ለማቅረብ እንደሚረዳም ሚኒስትር ዴኤታው አስታውቀዋል። በተጨማሪ ድጋፉ የመኖ ዘር ለማቅረብ፣ እንስሳት በሽታን መቋቋም እንዲችሉ የሚረዱ መድኃኒቶችና ክትባት ለመግዛት እና ለእርሻ ስራ የሚውል የሰብል ዘር ለመግዛት እንደሚያገለግል አስረድተዋል። ሚኒስትር ዴኤታው እንዳስታወቁት፤ ለሶስት ዓመታት በድርቅ የተጎዱ አርብቶ አደር አካባቢዎችን በመከታተል የገንዘብም ሆነ የዓይነት ድጋፍ ሲደረግ ቆይቷል።

በቀጣይ ግብርና ተኮር ሰፋፊ ፕሮጀክቶችን በማከናወን በድርቅ የሚጠቁ አካባቢዎች ላይ የሚከሰቱ ችግሮችን በዘላቂነት መቋቋም ይገባል። ግብርና ሚኒስቴርም በድርቅ የተጠቁ አካባቢዎች ላይ ሰፋፊ ፕሮጀክቶችን በማዘጋጀት ቀጣይነት ባለው መልኩ ለመስራት ዝግጁ ነው ሲሉ ዶክተር ፍቅሩ ጠቁመዋል።

## የውጭ ቀጥታ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ለመሳብ ያልተቀረፉ ችግሮች መኖራቸውን የገለጹት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ኢትዮጵያ ወደ ምትፈልገው የኢኮኖሚ ዕድገት እንድትገባ በዘርፉ ያሉ ችግሮችን ለይቶ መፍታት ጊዜ ሊሰጠው የማይገባ ጉዳይ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

እንደ አቶ ደመቀ ገለፃ፤ ኮንትሮባንድን በተመለከተ ኮሚቴ ተዋቅሮ የተሠሩ ሥራዎች ቢኖሩም የግብርናና የተለያዩ የሀገር ውስጥ ምርቶች በሕገወጥ መንገድ ወደ ውጭ ይላካሉ። በዚህም ኢትዮጵያ ከፍተኛ የሆነ ኪሳራ እየደረሰባት ነው። ይህንን ለመቆጣጠር የሚመለከታቸው አካላት በጋራ መሥራት ይኖርባቸዋል።

በተጨማሪም ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ በሕገወጥ መንገድ የሚገቡ ምርቶች በመኖራቸው በሀገር ኢኮኖሚ ላይ ጉዳት እያደረሰ በመሆኑ በቅንጅት መሥራት እንደሚገባም ገልጸዋል።

በቀጣይ ኮንትሮባንድን ለመከላከል በቅንጅት በመሥራት የሀገር ኢኮኖሚን ለማሳደግ ጥረት ይደረጋል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ኮንትሮባንድ የሀገር ኢኮኖሚን እየጎዳ በመሆኑ በትብብር መሥራት አስፈላጊ ነው። የውጭ ሀገራት በኢትዮጵያ ሀብት እየበለጸጉ ነው። በመሆኑም በኢኮኖሚው ያሉ ችግሮችን በመለየት መፍትሄ ለማበጀት እንደሚሠራ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ኮሚሽነር ሌሊሴ ነሚ በበኩላቸው፤ የሀገራችን ኢንቨስትመንት ሁኔታ ባለፈው ሰባት ወራት ከውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ወደ ሁለት ነጥብ 25 ቢሊዮን መሳብ ተችሏል። ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር የ 16 ነጥብ አምስት በመቶ ዕድገት አሳይቷል።

በሀገሪቱ የሰላም ስምምነት ከተካሄደ በኋላ የተለያዩ ሀገራት በኢትዮጵያ ያለውን ኢንቨስትመንት ሁኔታና አቅም ለመረዳት እየመጡ ነው። በተለይ የቻይና፣ ፓኪስታን እና የህንድ የኢንቨስትመንት ሉዑካን ቡድኖች ተጠቃሽ ናቸው ብለዋል።

ኢትዮጵያ ለኢንቨስትመንት ምቹ ናት ያሉት ኮሚሽነሯ፤ ብዙ የመልማት አቅም እንዲሁም የገበያ መረዳረሻዎች አሏት ብለዋል።

ይሁንና የአሠራር ችግሮችን መፍታት አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመው፤ በተለይ የመሬት አቅርቦት ችግርን መፍታትና ኢንቨስተሮችን መሳብ አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል። በተጨማሪም የሕግና የፖሊሲ ለውጦችን ማድረግ እንደሚያስፈልግ ገልጸው፤ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ችግሮችን መፍታት እንደሚገባ ገልጸዋል።

የመድረኩ ዓላማ የኢንቨስትመንት፣ የቱሪዝም፣ የውጭ ንግድ፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርን በተቀናጀ መልኩ በመገምገም አቅጣጫ ማስያዝ ነው ተብሏል።

## ለ250 ሺህ ምሩቃን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ፈተናውን በአግባቡ መስጠት እንዲቻል ከመንግሥትና ከግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር በቅርበት በመሥራት ላይ መሆኑን ገልጸው፤ በዚህም ፈተናውን በአግባቡ ለመስጠትና ተማሪዎችም ተዘጋጅተው ፈተናውን እንዲሰሩ የሚያግዙ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች በመሠራት ላይ ናቸው ብለዋል።

የመውጫ ፈተናውን ወስደው ማለፍ ያልቻሉ ተማሪዎች ደጋግመው መፈተን የሚችሉበት ዕድል መኖሩን ገልጸው፤ ደጋግሞ ተፈትኖ ፈተናውን ማለፍ ያልቻለ ተማሪ ከዲግሪ በታች ባሉ ደረጃዎች ምዘና ወስዶ መቀጠል እንዲችል የሚያደርግ የብቃት ማረጋገጫ ማዕቀፍ በትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን በመዘጋጀት ላይ ነው። ሆኖም ተፈታኙ ለዩኒቨርሲቲ መውጫ ፈተና ዝግጁ ነኝ ብሎ ባሰበ ጊዜ ፈተናውን መውሰድና የዲግሪ ማረጋገጫ ማግኘት ይችላል ነው ያሉት።

ፈተናው በኦንላይን እንደሚሰጥ ያመለከቱት አቶ ሰይድ፤ ለዚህ ያመች ዘንድም የሶፍትዌር ማዘጋጀትን ጨምሮ ፈተናውን በስኬት መስጠት የሚያስችሉ ሥራዎች በመሠራት ላይ ናቸው። ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋርም በቅርበት እየተሠራ ነው።

ፈተናው ደረጃውን የጠበቀና ከሰው ንክኪ ነጻ እንዲሆን በትኩረት እየተሠራ ነው። ተማሪዎችንም በአግባቡ የሚመዝን እና ለስርቆት ምንም አይነት ዕድል የማይፈጥር እንዲሆን ይደረጋል ብለዋል።

ተማሪዎች ዋናውን ፈተና ከመፈተናቸው በፊት ሞዴል ፈተናዎችን እንደሚወስዱ ጠቅሰው፤ ይህም ያለባቸውን ክፍተት ለይተው እንዲዘጋጁና ፈተና የሚሰጥበትን ሶፍትዌር እዲለማመዱ ዕድል እንደሚፈጥርላቸው ተናግረዋል።

የዩኒቨርሲቲ መውጫ ፈተናው በስኬት እንዲጠናቀቅ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጀምሮ ተቋማት፣ መምህራን፣ ተማሪዎችና ወላጆች የሚጠበቅባቸውን ሚና መወጣት አለባቸው ያሉት ኃላፊው፤ ተማሪዎች በተቀመጠው ደረጃ መሠረት ፈተናውን ለማለፍ በአግባቡ መዘጋጀት አለባቸው። የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም የተማሪዎችን ክፍተት በአግባቡ ለይተው አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ እንዳለባቸው መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ታማኝ ግብር ከፋዮች የአገራዊ ብልፅግና ጉዞ መሰረት ናቸው!

ግብር በዘመናዊው ዓለም የመንግስትን መመስረት ተከትሎ ተግባራዊ መሆን እንደ ጀመረ የታሪክ መዛግብት ይጠቁማሉ። እስከ ዛሬም የተለያዩ ምዕራፎችን አልፎ ለመንግስታት ዋነኛ የጥንካሬ ምንጭ የሆነበት ደረጃ ላይ ደርሷል።

በእኛም አገር የመንግስት ምስረታ ካለው የረጅም ዘመን ታሪክ አንጻር፤ የግብር ጉዳይ በተመሳሳይ መልኩ የሚታኝ ቢሆንም፤ አሁን ላይ ያለበት ሁኔታ ግን እጅግ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ካሉ አገራት ምድብ የሚያስቀምጣት ነው።

አንድም በማኅበረሰቡ ውስጥ ስለ ግብር ያለው አመለካከት የተዛባ መሆን፤ ይህንን የሚገራ የአስተሳሰብ ግንባታ በስፋትና በጥልቀት አለመካሄዱ፤ ግብርን ፍትሀዊና ዘመናዊ በሆነ መንገድ መሰብሰብ የሚያስችል አገራዊ ስርአት መፍጠርና መተግበር አለመቻሉ እና ሙስና ለችግሩ ዋነኛ ተጠቃሽ ምክንያቶች ናቸው።

ከዚህም የተነሳ በአገሪቱ የግብር ስወራ እንደ አንድ መሰረታዊ ችግር የሚጠቀስ ከሆነ ውሎ አድሯል፤ በዚህም በቢሊዮን የሚቆጠር በግብር መልክ ሊሰበሰብ የሚችል ሃብት ሳይሰበሰብ እየቀረ ስለመሆኑም የተለያዩ መረጃዎች ያመለክታሉ።

ግብር በአግባቡ ያለመሰብሰቡ በልማት ውጥኖች አፈጻጸምም ላይ አሉታዊ ጥላ ሆኗል። አሁን ላለው የሕዝባዊ አገልግሎት ክፍተትም ሆነ ድህነት እንደ አንድ ምክንያት የሚጠቀስ ነው።

ይህንን አገራዊ ችግር ለመፍታት ከለውጡ ማግስት አንስቶ ከግብር ጋር የተያያዙ አሰራሮችን ከማዘመን ጀምሮ በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለውን የተዛባ የግብር አስተሳሳብ ለማረቅ የሚያስችሉ ስራዎች በስፋት እየተሰሩ ነው። በዚህም እየተስተዋለ ያለው ለውጥ የሚበረታታ ነው።

በተለይም ከፍተኛ ግብር ከፋይ የሆኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚጠበቅባቸውን ግብር በአግባቡና በታማኝነት እንዲከፍሉ ለማስቻል፤ የሚካሄዱ የማነቃቃት/የማነሳሳት ስራዎች በተጨባጭ እያስመዘገቡት ያለው ውጤት ተስፋ ሰጭ ነው።

ለዚህም ባለፈው እሁድ የአዲስ አበባ ገቢዎች ቢሮ "ግብር ለአገር ክብር" በሚል መሪ ቃል በ2014 ዓ/ም በጀት ዓመት ሞዴል ግብር ከፋዮች ለሆኑ 300 ግብር ከፋዮች የሰጠው ዕውቅና የዚሁ እውነታ ማሳያ ነው።

ቢሮ በወቅቱ እንዳስታወቀው፤ በበጀት ዓመቱ ሰባት ወር ለመሰብሰብ ካቀደው 59 ነጥብ 11 ቢሊዮን ብር ውስጥ 58 ነጥብ 43 ቢሊዮን ብር መሰብሰብ ችሏል። ይህም ከእቅዱ 98 ነጥብ 8 ከመቶ ነው።

በመርሀ ግብሩ እውቅና የተሰጣቸው ከ56745 ግብር ከፋዮች ውስጥ 300 የሚሆኑት ናቸው። እውቅና የተሰጣቸውም ትክክለኛ መረጃዎችን በጊዜው አሟልተው በመገኘታቸው እንደሆነ ታውቋል።

በርግጥ ከግብር ከፋዩ ቁጥር፤ አስፈላጊውን መረጃ በትክክል እና በጊዜው አሟልተው ከተገኙት ግብር ከፋዮች አንጻር በዘርፉ ያለው እውነታ ብዙ መስራት እንደሚያስፈልግ አመላካች ቢሆንም፤ ከመጣንበት የተበላሸ የግብር አሰባሰብ መንገድ አኳያ ያለውን እያበረታቱ መጓዝ የግድ ነው።

በተለይም አዲስ አበባ እንደ ስሟ ሁሌም አዲስ እንድትሆን የሚደረገው ጥረት ስኬታማ የሚሆነው በከተማዋ ያሉ ግብር ከፋዮች የሚጠበቅባቸውን ግብር በአግባቡ መክፈል ሲችሉ ብቻ ነው። ለዚህ ደግሞ ግብር ከፋዩ ኅብረተሰብ በታማኝነት ግብር በመክፈል ራሱንና መላውን ኅብረተሰብ እያገለገለ መሆኑን በአግባቡ ሊረዳ የሚችልበትን ዕድል መፍጠር ወሳኝ ነው

የከተማዋ ነዋሪም ቢሆን መንግስት ሕዝባዊ አገልግሎቶችን በሚፈለገው መልኩ ማቅረብ የሚችለውና ልማት የሚፋጠነው ከግብር በሚሰበሰበው ሀብት መሆኑን በሚገባ ተረድቶ፤ ግብር በአግባቡ ለመሰብሰብ በሚደረገው ጥረት ንቁ ተሳታፊ ሊሆን ይገባል። ይህንን ማድረግ የተሻለች ከተማ ለመጭው ትውልድ የመፍጠር ያህል ከፍያለ ሕዝባዊ ተልእኮ መሆኑንም ሊያስተውል ይገባል!

**አዲስ ዘመን**
ኢፕድ
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን
**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ብልፅግናን በተሻለ መልኩ ማረጋገጥ የሚቻለው…

አስናቀ ፀጋዬ

ደብረሲና ከአዲስ አበባ በ200 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ በሰሜን ሸዋ ዞን ስር ያለች ከተማ ናት።ከተማዋ በከፍታ ቦታ ላይ የምትገኝ እንደመሆኗ በጣም ቀዝቃዛ ናት።በዚሁ ቅዝቃዜዋ ምክንያት የከተማዋ ነዋሪዎች ጃኬቱንም፤ ሹራቡንም ፎጣውንም ደራርበው ነው የሚለብሱት።ነዋሪዎቹ ቅዝቃዜውን በልብስ ብቻ መከላከል ስለማይችሉ በጥሩ ሁኔታ እንደተዘጋጀች የሚመሰክሩላትን ካቲካላ ይጎነጯሉ።ይህች ካቲካላ ከእነርሱ ተርፋ ከተማዋን አቋርጠው ለሚያልፉ መንገደኞችም ለገበያ ትቀርባለች።ከተማዋ ከደብረብርሃን ቀጥሎ ያለች ከተማ እንደመሆኗና ወደቀጣዩ ከተማ እንደመስፈንጠሪያ ሆና ስለምታገለግል ሞቅ ያለች ናት፡፡

ከደብረሲና በቅርብ ርቀት ላይ ወደ ምትገኘው ሸዋሮቢት የተጓዘ ሰው አንድ ነገር ያጤናል።በሁለቱ ከተሞች መካከል ያለው ርቀት 20 ኪሎ ሜትር ብቻ ነው።የሚያስደንቀውና ሊስተዋል የሚገባው ጉዳይ ግን በከተሞቹ መካከል ያለው ቅርብ ርቀት አይደለም።ይልቁንም ከቅዝቃዜ እልም ወዳለ ሙቀት መግባት እንጂ።ከደብረሲና ወደ ሸዋሮቢት ሲጓዙ 20 ኪሎሜትሩን በቅጡ እንኳን ሳያጨሱ በብርድ እየተንዘፈዘፉ በቅፅበት ወደ ጋለ ሙቀት ይገባሉ።ገና ብርዱ ሳይለቅዎ በላብ ይጠመቃሉ።በቅዝቃዜ የተኮማተረው ሰውነትዎ ሳይፍታታ በሙቀት ልብዎ ቅልጥ ይላል።

ይህ ድንቅ የተፈጥሮ ክስተት ቢሆንም በኢትዮጵያ ባለፉት አምስት ዓመታት ውስጥ የተከሰቱትን ነገሮች ሁሉ የማያይዘው ከዚህ ተፈጥሯዊ እውነት ጋር ነው። በኢትዮጳያ ከዛሬ አምስት ዓመት በፊት ለውጡ እንደመጣ በተለይ በመጀመሪያው ዓመት በርካታ አበረታችና ተስፋ ፈንጣቂ ስራዎች ተሰርተዋል።ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ለመጀመሪያ ግዜ ፓርላማ ቀርበው ንግግር ሲያደርጉ የኢትዮጵያን ስም ደጋግመው በመጥራታቸው የብዙዎችን ልብ ማሞቅ ችለዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ስራቸውን ‹‹ሀ›› ብለው ከጀመሩ በኋላ በቀድሞው መንግስት በፖለቲካ አመለካከታቸው ምክንያት ታስረው የነበሩ እስረኞችን በመፍታታቸው፣ በውጪ ሆነው ሲታገሉ የነበሩ የፖለቲካ ድርጅቶች ወደአገር ውስጥ እንዲገቡ በማድረጋቸው ከምንም በላይ ደግሞ ከኤርትራ ጋር የነበረውን የቆየ ቁርሾ በመፍታታቸው በህዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነትና ምስጋና አግኝተዋል።በዚህም ከኖቤል ሽልማት ድርጅት በሰላም ዘርፍ ተሸላሚ ለመሆን በቅተዋል።

እነዚህን ሁሉ ተስፋ ሰጪ ተግባራትን ህዝቡ በወጉ እንኳን ሳያጣጣጥም ወዲያው ነበር እዚም እዚያም ኮሽታ መስማት የጀመረው።ልክ እንደ ደብረሲና ሸዋሮቢት ጉዞ ነበር አገሪቱ ከቅዝቃዜ ወደ በርሃ/ሙቀት/ የገባችው።በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ብሔርን መሰረት ባደረጉ ግጭቶች ብዙዎች ሞተዋል፣ በርካቶች ደግሞ ተፈናቅለዋል።የዛኑ ያህል ደግሞ በአገሪቱ ታሪክ ታይተውም ሆነው ተሰምተው የማያውቁ አሰቃቂ ግድያዎች በዜጎች ላይ ተፈፅመዋል።በተመሳሳይ ሃይማኖትን መሰረት ያደረጉ ግጭቶችም ተከስተው አብያተ ክርስቲያናት ተቃጥለዋል፣ መስጂዶችም ፈርሰዋል።በዚሁ ሳቢያ ሰዎችም ለህልፈት ተዳርገዋል።

እንዲህ እያለ በፍጥነት እየተጋጋለ የመጣው የአገሪቱ ሁኔታ ይበልጥ ተባብሶ በመንግስትና በሕወሓት መካከል ወደሚደረግ ጦርነት አመራ።በዚሁ የእርስ በርስ ጦርነት ምክንያት በሁለቱም በኩል በርካታ ሰዎች አልቀዋል።ንፁሃን ዜጎች በግፍ ተጨፍጭፈዋል።ሴቶች ተደፍረዋል።ብዙሃኑም ተፈንቅሎ ለርሃብና ጥማት ተዳርጓል።ያ ሁሉ ሰው አልቆ ግን አብዛኛዎቹ ጦርነቶች በስምምነት እንደሚጠናቀቁ ሁሉ በመንግስትና በሕወሓት መካከል ለሁለት ዓመት የተደረገው ጦርነት የተቋጨው በፕሪቶሪያ ስምምነት ነበር፡፡

በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንን በኩል የእምነቱን ተከታዮች የልብ ትርታ ለማረጋገጥና ፖለቲካውን በእምነቱ ውስጥ ለማስገባት የተደረገው ጥረት ከሰሜኑ ጦርነት በኋላ በአገሪቱ የተከሰተ ሌላኛው ትኩሳት ነው። እንግዲህ ይህ ሁሉ የሆነው በአምስት ዓመት ውስጥ ነው።በነዚህ አምስት ዓመታት ውስጥ ያልተደረገ ነገር የለም።ነገሩም የሆነው በላይ በላይ ነው።ልክ እንደ ደብረሲና ሸዋሮቢት መንገድ ሁሉም ነገር ከተራጋጋውና ከተቀዛቀዘው ወደ ሙቀትና ግለት ውስጥ ገብቷል።የእርሰ በርስ ንትርኩ፣ የፖለቲካው ሽኩቻ፣ ሞትና መፈናቀል አሁንም አለ። በዛ ላይ ደግሞ የኑሮ ውድነቱ አይሎ ህዝቡ ከሚሸከመው ጫንቃ በላይ ሆኗል።

**አሁን መንግስት ለኑሮ ውድነት ቅነሳ ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራ ይገባል። የስራ አጥ ቁጥሩም ከግዜ ወደ ግዜ እየጨመረ በመምጣቱ በአነስተኛ ፕሮጀክቶችና በተለያዩ የስራ መስኮች ዜጎች ተቀጥረው የሚሰሩበትንና ገቢ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት። ከሁሉ በላይ ደግሞ በተለይ ወጣቶች የራሳቸውን ስራ በመፍጠር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከመንግስት በኩል የቦታና የገንዘብ ድጋፍ በስፋት መቅረብ ይጠበቃል**

በርግጥ መንግስት ሲለወጥ የሽግግር ወቅት ያስፈልጋል።ህዝቡም ይህንኑ በመረዳት ለአዲሱ መንግስት ግዜ ሰጥቷል።እንደውም ገዢው ፓርቲ ብልፅግና እንዲመራው ይሁንታውን በምርጫ አረጋግጧል።ከነገ ዛሬ ነገሮች ይሻሻላሉ ብሎ ያለውን ታጋሽነት ለመንግስት አሳይቷል።አሁንም እንዲሁ፤ ይህም ሆኖ ግን የሰላም ችግር አሁንም አገራዊ አጀንዳ ነው። ሰላም መጣ ሲባል ዳግም ይደፈርሳል።የተስፋ ጭላንጭል ታየ ሲባል መልሶ ይጨልማል።በዚህ ላይ የኑሮ ውድነቱ ተደምሮበት ሕዝቦች ችግሮች ውስጥ ይዋልላሉ።

አሁን መንግስት ለኑሮ ውድነት ቅነሳ ትኩረት ሰጥቶ ሊሰራ ይገባል። የስራ አጥ ቁጥሩም ከግዜ ወደ ግዜ እየጨመረ በመምጣቱ በአነስተኛ ፕሮጀክቶችና በተለያዩ የስራ መስኮች ዜጎች ተቀጥረው የሚሰሩበትንና ገቢ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት።ከሁሉ በላይ ደግሞ በተለይ ወጣቶች የራሳቸውን ስራ በመፍጠር ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከመንግስት በኩል የቦታና የገንዘብ ድጋፍ በስፋት መቅረብ ይጠበቃል፡፡

ዘላቂ ሰላም በመላ አገሪቱ እንዲመጣ ከሁሉም በላይ አቅሙን አቀናጅቶ መስራት ይጠበቅበታል። ዜጎች በሰላም ወጥተው፤ ሰርተውና ነግደው በሰላም እንዲገቡ ደህንነታቸውንና የመኖር ዋስትናቸውን ማስጠበቅ ይኖርበታል። በጥቅሉ መንግስት ቅድሚያ ሊሰጣቸው በሚገቡ የሰላም፣ የመኖር ዋስትናና የኑሮ ውድነት ማሻሻያ ላይ ይበልጥ ትኩረት አድርጎ መስራት ይጠበቅበታል። እንዲህ ሲሆን ነው ብልፅግናን በተሻለ መልኩ ማረጋገጥ የሚቻለው!!

# ነፃ ሀሳብ



ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

# የክፍለ ዘመናችን ታላቅ ግኝት

**(የመጨረሻ ክፍል)**

እንደማንኛውም ግዙፍና አጓጊ ፕሮጀክት የጄምስ ዌብ የህዋ ቴሌስኮፕም በብዙ ውጣ ውረዶችና ፈተናዎች አልፏል ትለናለች ናዲያ፤ የተያዘለት በጀት በ20 እጥፍ ማደጉ፣ በስምንት ዓመት ይጠናቀቃል ሲባል 30 ዓመት መውሰዱ፤ ከመነሻ ሀሳቡ፣ ዕቅዱ፣ ዲዛይኑ፣ ግንባታውና እስከመጠቀበት ጊዜ ድረስ እውን ይሆን በሚል በጥርጣሬ ያዩት የነበሩ፤ ተቋማት፣ ፖለቲከኞች፣ ሊቃውንት፣ ወዘተረፈ ቁጥርም ቀላል አልነበረም። የሀብል ቴሌስኮፕም ተመሳሳይ እጣ ገጥሞት ነበር ስትል ታስታውሰናለች ጸሐፊዋ።

በዌብ ቴሌስኮፕ ንድፍ የተሳተፈው ጆን ኦሚያራ፤ ሲያጉረመርሙ የነበሩ ሁሉ የዌብን የመጀመሪያ የህዋ ምስል ሲያዩ ይረሱታል እንዳለው፤ ዛሬ ሕዝበ አዳም ሲያዘንበው የነበረውን ያን ሁሉ ትችት እረስቶ ቃላት እስኪያጥረው አድናቂ ሆኖ አርፎታል። አጽናፈ ዓለም እጅጉን ረቂቅ፣ ጥልቅ፣ መጀመርያ እና መጨረሻ የሌለው አልፋ እና ዖሜጋ ነው። የምድርን ግዝፈት፣ የተፈጥሮ ረቂቅነት፤ እየኖርንባት፣ እያየናት፣ እየጨበጥናት፣ እያሸተትናት እና እየቀመስናት በእርግጥ ገና በቅጡ አላወቅናትም ይለናል የጀርመኑ ሬዲዮ ዶቸ ቬሌ ደግሞ።

ይህ በእንዲህ እያለ ታዲያ እንዴት ተደርጎ ከእኛ በብርሃን ዓመታት ርቀው የሚገኙ ዓለማትን መመርመርስ ይቻለናል፤ ለዚያውም መቶ ሚሊዮን ዓመታትን ወደ ኋላ ተመልሶ ፍጥረተ ዓለምን ለማወቅ በውኑ ይቻላልን ? የሚሉ ጥያቄዎች ከዚህም ከዚያም እየተነሱ ነው። ጋዜጠኛ እና የስነፈለግ ተመራማሪ የሆነችው ኤልሳቤት ቤርሶን በበኩሏ በጀምስ ዌብ ላይ ያላትን ምልከታ ስትናገር፤ በእድሜዬ የሰው ልጅ በጠፈር ምርምር ረገድ ያሳየውን እመርታ ማየት ችያለሁ። ቴሌስኮፑ እየላካቸው ያሉ ምስሎችም ለዚህ ምስክሮች ናቸው። ሰዎች በዙርያቸው ባለው ሕዋ ውስጥ ምን እየተካሄደ እንዳለ የማወቅ ጉጉታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ባለበት ሰዓት ቴሌስኮፑ መምጠቁ ጥሩ አጋጣሚ ነው ትላለች።

በ18 ጠንካራ እና ግዙፍ ወርቃማ መስታወቶች የተሠራችው እና እንደ ጎርጎርሳዊው አቆጣጠር፤ ከ1961 እስከ 1968 የአፖሎ 11ን የህዋ ጉዞ ተልዕኮ በመራው ጀምስ ኤድዊን ዌብ ስም የተሰየመው ቴሌስኮፑ፤ በአንድ ነጸብራቀ ምስል ተቀባይ መሳርያ አማካኝነት እጅጉን ርቆ ምናልባትም እስካሁን ከተደረሰባቸው መረጃዎች፤ አንድ እርምጃ የተራመደ መደምደሚያ ላይ ሊያደርሱ የሚችሉ መረጃዎችን ይሰበስባል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበታል።

ጀምስ ዌብ በህዋ ውስጥ የሚደርስበትን ሙቀት ቅዝቃዜ፤ ግጭት ተቋቁሞ ሚሊዮን ኪሎ ሜትሮችን አቆራርጦ ስፍራውን ይዟል። የወዲያኛውን ዓለም አቅርበው ለማየት የቋመጡ የሰው ልጅ ዓይኖች በቴሌስኮፑ ዓይኖች ላይ ተስፋቸውን ጥለዋል። በአጽናፈ ሰማያት መሐል ባለችው ትንሿ መሬት ላይ ብቻችንን ነን ወይስ እኛ የማናውቃቸው ሰማየ ሰማያትን ተሻግረው ሌሎች ይኖሩ ይሆን ? የሚለውንና ከፍ ብሎ የተጠቀሱ ጥያቄዎችን ይዞ ጉዞውን ያጠናነቀው ቴሌስኮፕ ምላሽ ይኑረው አይኑረው ወደፊት የሚታይ ነው።

ቀናት ፤ ወራት ምናልባትም ዓመታት ልንጠብቅ ግድ ሊለን ይችል ይሆናል። ደግሞስ ማን ያውቃል፤ ይሄ ትውልድ የጠየቀው ጥያቄ መልስ ሳያገኝ ትውልድ ሄዶ ትውልድ ሊመጣ ይችላል ይለናል ዶቸ ቬሌ። ግዙፉ ቴሌስኮፕ በጠፈር ላይ ያሉ ከዋክብትን ይቃኛል። ይመረምራል። የማይታወቁ ፕላኔቶች ያስሳል። ከምድራችን ውጭ በሌላ ፕላኔት ህይወት ያለው ነገር መኖሩን ወይም ለሰው ልጅ መኖሪያ ሊሆን የሚችል ሌላ ፕላኔት እንዳለ ይፈትሻል ይለናል የእንግሊዙ ዜና

> **ት**ውልደ እንግሊዛዊው አሜሪካዊ ፈላስፋ ቶማስ ፔይን በ18ኛው ክፍለ ዘመን እንደ ነብያት ቀድሞ ተገልጦለት ኖሮ፤ " አዲሱን ዓለም ልናዋልድ እየተዘጋጀን ነው። " ብሎ ነበር፤ ያለውም አልቀረም። አሜሪካ የአዳዲስ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የፈጠራ ምድር በመሆን አዲሱን ዓለም፤ 3ኛውን የኢንዱስትሪ አብዮት ስትገላገል፣ ስትወልድ፤ በተቃራኒው አውሮፓ ግን እንደ ባዝራ መካን ከመሆኗ ባሻገር በጥልቅ እንቅልፍ ላይ ናት

ማሰራጫ ቢቢሲ።

በአይነቱ የመጀመሪያ የሆነው የዌብ ቴሌስኮፕ በአጽናፈ ዓለም እስከ ዛሬ ያልታዩ አዳዲስ ጋላክሲዎችንና ፕላኔቶችን ያገኛል ተብሎ ይታመናል። ይህ ጹሑፍ እየተጠናቀረ ባለበት እንኳ በረዷማ የሆነ ጭጋግ እና ካርበን ዳይኦክሳይድ መገኘቱ እየተነገረ ነው። አጽናፈ ዓለም በታላቅ ፍንዳታ/ቢግ ባንግ/ ነው የተፈጠረው የሚለውን ሳይንሳዊ ንድፈ ሀሳብ የሚያጠነክር ወይም የሚቃረን ፍንጭ ይሰጣል የሚል እምነትም ተይዟል።

የጄምስ ዌብ ቴሌስኮፕ ከትሮፒካል ሬይን ፎረስት ተነስቶ አጽናፈ ዓለም ተፈጥሮበታል ተብሎ በሳይንቲስቶች የሚታመንበትንና፤ የሁሉ ነገር መጀመሪያ የሆነውን ቢግ ባንግ በቅርብ መመርመር ወደ ሚያስችልበት የህዋ አካል መጥቋል ይላል ቢቢሲ። የጄምስ ዌብ የጠፈር ቴሌስኮፕ ዋና ዋና ዓላማዎች ፤ የመጀመሪያው ከቢግ ባንግ በኋላ በአጽናፈ ዓለም/ዩኒቨርስ/ ውስጥ የተፈጠሩትን፤ የመጀመሪያዎቹን ከዋክብትና ጋላክሲዎች ይመረምራል። ሁለተኛው የጋላክሲዎችን አፈጣጠር እና ዝግመተ ለውጥ ማጥናት እና፤ የፕላኔቶችን ስርዓቶች እና የህይወት አመጣጥን ማጥናት ሶስተኛው ይገኝበታል።

ቴሌስኮፑ እስካሁን ከተገኙ እጅግ በጣም ርቀው የሚገኙትን ሁለቱን ጋላክሲዎች ከማስመልከቱ ባሻገር፤ የጄምስ ዌብ የጠፈር ቴሌስኮፕ ከቢግ ባንግ በኋላ ከተፈጠሩት የመጀመሪያዎቹ ጋላክሲዎች አንዱን አሳይቷል። ቴሌስኮፕ በ32 ሚሊዮን የብርሃን ዓመታት ርቀት ላይ“የ ghost ጋላክሲን”ምስል ከማንሳቱ ባሻገር አዳዲስ ግኝቶችን ይፋ እያደረገ ነው ይለናል የእንግሊዙ የዜና ማሰራጫ ቢቢሲ።

በነካ እጃችን አጠቃላይ የሰውን ልጅ አኗኗር ፍጹም ሊቀይር ስለተዘጋጀው እና ሌላው የ21ኛው መክዘ ክስተት ስለሆነው በ2030 እኤአ ለዓለም ኢኮኖሚ 15 ትሪሊየን ዶላር ይጨምራል ተብሎ ስለሚጠበቀው የሰው-ሰራሽ ክህሎት ወይም አስተውሎት በዚያ ሰሞን ለንባብ የበቃው የTIME መጽሔት የሰው ልጅ ላለፉት 300,000 ዓመታት ኑሮውን ያቀለሉ ፈጠራዎችን ሲያከናውን የመጣ ቢሆንም ሰው ሰራሽ አስተውሎት ግን ወደ አዲስ ምዕራፍ እያሸጋገረው ነው ይለናል። ስዕል መሳል፣ ለኢሜላችን መልስ መስጠት፣ የታክስ ክፍያዎቻችንን፣ የጤና የምክር አገልግሎት፣ እንደ ተማሪ ፈተና ይቀመጣል፣ መጣጥፍ ይጽፋል፣ ወዘተረፈ አይነት አገልግሎቶችን እየሰጠ ይገኛል።

አርቲፊሻል ኢንተለጀንት (AI) ፡- ከሰው ልጅ አስተሳሰብ ባህሪዎች ጋር ተመሳሳይ የስራ አይነቶችን መፈፀም ችሎታ ያለው ውቅርን የሚያመለክት በውስጡ ሰፊ ሀሳብ ያለበት ሀረግ ነው ። ከጥንት ጊዜያት ጀምሮ የሰው ልጆች አንዳንድ እንደነዚ አይነት ክህሎት የማበልፀግ ፍላጎት ነበራቸው። የዘመናዊ ሳይንስ ማደግ ጋር ተከትሎ፤ የ AI ፍለጋው በሁለት ዋና ዋና አቅጣጫዎችን ወስደውታል: ሥነ ልቦናዊ ጥናት (psychological) እና ፊዚዮሎጂ (physiological) ጥናት በሰው አስተሳሰብ ተፈጥሮ፣ እና እንዲሁም ከጊዜ ወደ ጊዜ ይበልጥ የተራቀቁ የኮምፒዩተር ሥርዓቶች የቴክኖሎጂ እድገት ተፈጠረ። በሌላ አገላለፅ የ AI ቃል ትክክለኛውን የሰው አስተሳሰብ እውቀት አኳያ የራቀ ቢሆንም እንኳን ቀጥተኛ ከሆኑት ፕሮግራሚንግ የበለጠ ውስብስብ ተግባሮችን መፈፀም የሚችሉ የኮምፒውተር ስርዓቶች እና ፕሮግራሞች ላይ ተግባራዊ የሚሆን ነው።

በዚህ መስክ በጣም አስፈላጊው የምርምር ዘርፎች ውስጥ የመረጃ ማቀነባበር ሂደት፣ የንድፍ ቅደም-ተከተሎችን መረዳት፣ የኮምፒውተሮች ጌም-መጫወቻ (game-playing) እና ተግባራዊ መስኮች እንደ የሕክምና ምርመራ የመሳሰሉት ናቸው። በመረጃ ማቀነባበር አሰራር ሂደት አሁን ያለው ጥናት ኮምፒውተር አንድን የተጻፈ ወይም የንግግር መረጃን እንዲረዳ እና አጭር ማጠቃለያዎችን እንዲያደርግ፣ የተወሰኑ ጥያቄዎችን እንዲመልስ ወይም የዚህን መረጃ የተወሰኑ ስፍራዎች ውስጥ ለሚፈልጉ ተጠቃሚዎች መረጃን በሚያሰራጭ ፕሮግራሞች ላይ ያቀርባል።

ለእንደዚህ ያሉ ፕሮግራሞች እጅግ ወሳኝ የሆነው የስርዓቱ አቅም ሰዋሰዋዊ አረፍተ ነገሮች እንዲፈጠሩ እና በቃላት፣ ሀሳቦች እና ከሌሎች ሀሳቦች መካከል ትስስሮችን ለመመስረት ነው። ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የቋንቋ ሎጂካዊ አወቃቀር ለፕሮግራሙ የተሰጠው —የቃላት አገባብ—በዓረፍተ-ነገሩ ውስጥ፣ የትርጉም ችግር፣ ወይም የስነ-ፍቺ ጥናቶች (Semantics)፣ በእውነተኛው AI አቅጣጫ ውስጥ፣ በጥልቀቱ እርቀው የተቀመጡ ናቸው።

በሕክምናው ውስጥ፣ የበሽታ ምልክቶች፣ የህክምና ታሪክ፣ እና የታካሚውን ላቦራቶሪ ምርመራ ውጤቶች የሚተነትኑ፣ እና ከዚያም ለሐኪሙ የምርመራ ውጤትን የሚያመላክቱ ወይም ሀሳብ የሚያቀርቡ ፕሮግራሞች ተዘጋጅተዋል። የምርመራው ፕሮግራም እንደ ልዩ ባለሙያተኛ የሰው ልጅ የሆነበት መስኮች ውስጥ ልዩ ልዩ ስራዎችን ለማከናወን የተነደፉ ኤክስፐርት ስርዓቶች (Expert Systems) ተብሎ ለሚጠሩት ምሳሌ ናቸው።

የኤክስፐርት ስርዓቶች ኮምፒውተሮችን ከቀጥተኛ የፕሮግራሚንግ ስርዓት ባሻገር ባለ ደረጃ ላይ ይወስዱታል፣ ከመረጃዎች በመነሳት የሚወሰን ህግ-መሰረት (rule-based inference) ተብለው የሚጠራ ቴክኒክ ላይ መሰረት ያደረገ፣ ዴታን ለማቀነባበር የሚጠቅሙ ቀድሞ የተመሰረቱ የህግ ስርዓቶች ናቸው። እጅግ የተራቀቁ ቢሆኑም፣ ስርዓቶች አሁንም የእውነተኛውን የማሰብ ችሎታ ውስብስብ እውቀት ላይ ገና አልቀረቡበትም።

በርካታ የሳይንስ ሊቃውንት እውነተኛ AI ን ሊፈጠሩ እንደሚችሉ ጥርጣሬ አላቸው። የሰው ልጅ አእምሮ አሰራር ላይ ያለው ግንዛቤ አሁንም ገና አነስተኛ ነው፣ እና የኮምፒውተር ንድፍ የማይታወቁ እና ውስብስብ ሂደቶችን በተመሳሳይ ሁኔታ አመሳስሎ ለመተግበር ምን አልባት የአቅም ገደቦች አሉበት። የእውነተኛ AI ግብ ላይ ለመድረስ የተለያዩ መንገዶች በጥቅም ላይ እየዋለ ነው። አንዱ አቀራረብ ትይዩ የአሰራር ሂደት-አገናኝ እና ባንድ ጊዜ ጥምር የኮምፒውተር ተግባሮች የሚለውን ጽንሰ-ሀሳብ ተግባራዊ ማድረግ ነው። ታሪካዊ ዳራውን በአለፍ ገደም እንመልከት።

ትውልደ እንግሊዛዊው አሜሪካዊ ፈላስፋ ቶማስ ፔይን በ18ኛው ክፍለ ዘመን እንደ ነብያት ቀድሞ ተገልጦለት ኖሮ፤ " አዲሱን ዓለም ልናዋልድ እየተዘጋጀን ነው። " ብሎ ነበር፤ ያለውም አልቀረም። አሜሪካ የአዳዲስ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የፈጠራ ምድር በመሆን አዲሱን ዓለም፤ 3ኛውን የኢንዱስትሪ አብዮት ስትገላገል፣ ስትወልድ፤ በተቃራኒው አውሮፓ ግን እንደ ባዝራ መካን ከመሆኗ ባሻገር በጥልቅ እንቅልፍ ላይ ናት። ሲል ይሳለቃል ተነባቢው የየካቲት ወር መጨረሻ ዕትም The Economist መፅሔት፤ ይህ የአውሮፓ ድንዛዜ የሚገለፀውም በቴክኖሎጂ ዘርፍ ባስመዘገበችው ውጤት ነው።

ዛሬ በዓለማችን ቀዳሚ ከሆኑ 20 የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኩባንያዎች 15ቱ በአሜሪካ መገኘታቸው በአውሮፓ ግን አንድ ብቻ መሆኑ ለዚህ ጥሩ ማሳያ ነው። የአሜሪካው ሲሊካን ቫሊ የዓለማችን ባለ ምጡቅ አእምሮ የፈጠራ ሰዎችና ባለሀብቶች ሁል ጊዜ የሚቃጠሩና የሚገናኙበት ነው። በሲሊካን ቫሊ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ በየ6 ደቂቃው አዲስ ነገር ይፈጠራል። በሰዓት ሲሰላ 10፣ በቀን ሲመታ 240፣ በዓመት 87ሺህ 600 አዳዲስ ፈጠራ ማለት ነው። (እዚህ ላይ ለአፍታ አገራችን የምትገኝበትን ተጨባጭ ሁኔታ በምናብ አብራችሁኝ አሰላስሉና በመንፈሳዊ ቅናት እንድትንጨረጨሩ በአክብሮት እጋብዛለሁ ...!? ) ታዲያ ... ! አሜሪካ የቴክኖሎጂ ፈጠራ ምድረ ገነት ብትባል ይበዛባታል !? እረ ! በጭራሽ። በዓለማችን የመጀመሪያው የትሪሊዮን ዶላር ጥሪት አፕል መሆኑንም ይገነዘቧል።

ሆኖም አሜሪካ እነዚህ ኩባንያዎቿ የገመና* መብት the right of privacy እና የገበያ ውድድርን እንዲያከብሩም እየሰራች ነው። ፌስ ቡክ ገበያውን በበላይነት ስለተቆጣጠረ ወደ ትናንሽ ካምፓኒዎች መከፋፈል አለበት በማለት የምርጫ መቀስቀሻ እስከማድረግ ተደርሷል። የአውሮፓ ሕብረትም እጁን አጣጥፎ አልተቀመጠም። በ50ዎቹ IBM፣ በ80ዎቹ Micro Soft በምዕራባውያን ገበያን በበላይነት በመቆጣጠር monopoly እንደከሰሳቸው ሁሉ፤ ባሳለፍነው ወር ጉግልን የማስታወቂያ ነፃ የገበያ ውድድርን በማስተጓጎል የአውሮፓ ህብረት የ1 ነጥብ 7 ቢሊዮን ዶላር ቅጣት አከናንቦታል። ሕብረቱ በዚህ አያበቃም። በቀጣይ የቅጅ መብትን Copy Right፣ ዜጎች የግል መረጃቸው ባለቤትና የጥቅም ተጋሪ እንዲሆኑም እየሰራ ነው።

**ሻሎም !**
**አሜን ።**

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

# እንቦጭን በሳይንሳዊ መንገድ - ለኃይል አማራጭነት

**ጌትነት ተስፋማርያም**

የናይል ተፋሰስን ጨምሮ በበርካታ ሀገራት የሚገኙ ሐይቆችና ግድቦች ኢኮኖሚያዊ ጉዳት በሚያስከትሉ የውሃ ላይ መጤ አረሞች (water hyacinth) እየተጠቁ መሆናቸውን መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከእነዚህ መጤ አረሞች መካከል ደግሞ የእንቦጭ አረም (Eichhornia crassipes) ዋነኛው ጉዳት አድራሽ ነው።

እንቦጭ በስፔን ጓዲአና ወንዝ ተፋሰስ አካባቢና በዙምባብዌ ሃራሬ ከተማ አቅራቢያ በሚገኘው ቺቬሮ ሐይቅ ላይ በመንሰራፋት በብዝሀ ሕይወት ላይ ዘርፈ ብዙ ጥፋት አስከትሏል። በኢትዮጵያም በጣና ሐይቅ ላይ የተዛመተው አረሙ የሐይቁን ውሃ ከመምጠጥ ባለፈ የአሳ ሀብቱ እንዲቀንስ ብሎም የውሃ ላይ ትራንስፖርት እንዲስተጓጎል ምክንያት እየሆነ ነው።

መጤ አረሙ አባይ ወንዝ ከጣና ለቆ በሚወጣበት ጨረጨራ ግድብ አካባቢ ጭምር ከመከሰቱ ባለፈ በሌሎች አነስተኛ ግድቦችና ሐይቆች ላይም መጠኑን እያሰፋ መሆኑን የእጽዋት ሳይንስ ባለሙያዎች ያመለክታሉ።

ያደጉ አገራት አረሙን ለማጥፋት ለባዮ ኢነርጂ ግብዓትነትና ባዮፈርቲላይዘር ምርትነት፣ የአረሙን ተክል ለእጅ ስራና ለቤት ውስጥ መገልገያ ዕቃዎች በማዋል እንዲሁም ለእንስሳት መኖና ሌሎች መተግበሪያዎች ሲጠቀሙበት ይስተዋላል።

በኢትዮጵያም እንቦጭን የሚያጠፋ መድኃኒት አግኝቻለሁ የሚሉ ሰዎች በተለያዩ ጊዜያት ብቅ ብቅ ቢሉም ውጤታማነታቸው አሁንም ድረስ አጠያያቂ ሆኖ ቆይቷል።

በአማራ ክልል በተቋቋመው የጣና ሐይቅና ሌሎች የውሃ አካላት ጥበቃና ልማት ኤጀንሲ ባወጣው መረጃ በጣና ሐይቅ ላይ የተንሰራፋውን እንቦጭን የማጥፋቱ ሂደት በአብዛኛው በአርሶ አደሮችና በበጎ ፈቃደኛ ወጣቶች አማካኝነት በእጅ የመንቀል ስራ ላይ ያተኮረ ነው።

የሰው ኃይል በመጠቀም አረሙን በእጅ ማስወገድና በማሽነሪ የመጠቀም አማራጮች ሲተገበሩ ቆይተዋል። ለአረሙ ማስወገጃ ከውጭ አገራት በድጋፍ መልክ ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ማሽኖች ግን ደለል ባለባቸው የሐይቁ ዳር አካባቢዎች የበቀሉ እንቦጮችን በማጥፋት ረገድ ውጤታማ አልሆኑም። ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ በውሃ ላይ ተንሳፋፊ የሆኑት ማሽኖች በሐይቁ ዳር ያለው የውሃ ከፍታ በበቂ ሁኔታ እንዳይንቀሳቀሱ ስለሚያግዳቸው ነው።

በተለያዩ ዓለማት ተግባራዊ የሆነውና አዋጭ ሆኖ የተገኘው የመጤ አረም ማስወገጃ ስልት ደግሞ ስነ-ሕይወታዊ በሆኑ ባዮሎጂካል መንገዶች መጠቀም በተለይ መጤ አረሙን ማስወገድ ላይ ያተኮረ ነው። እንቦጭና መሰል የውሃ ላይ አረሞች እንዳይዛመቱ በባክቴሪያ፣ በፈንገስና በተለያዩ ተባዮች እንዲጠበቁ የሚደረግበት ሳይንሳዊ መንገድን ባደጉት አገራት ጥቅም ላይ ውሏል። በሌላ በኩል ደግሞ ኬሚካል በመጠቀም አረሙን የማጥፋት ስልትን ጥቅም ላይ ያዋሉ የአውሮፓ አገራት አሉ።

የተለያዩ አገራት በውሃ አካሎቻቸው ላይ የእንቦጭ አረም የሚያስከትለውን ጉዳት ለመቀነስ ኬሚካልን፣ ባዮሎጂካል ማጥፊያ መንገዶችንና በማሽን የመንቀል አማራጮችን በአንድነት ቢጠቀሙም ከአረሙ ስነ-ሕይወታዊ ባህሪ የተነሳ እንቦጭን መቆጣጠርና የሚዛመትበትን መጠን መቀነስ እንጂ ሙሉ በሙሉ ማጥፋት አዳጋች ሆኗል።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኬሚስትሪ ተመራማሪው ፕሮፌሰር ሽመልስ አድማሴ በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ የእንቦጭ አረም በውሃ አካላት ላይ የሚያደርሰው ጉዳት እየተባባሰ መምጣቱን በመጥቀስ የአረሙን የመዛመት ሂደት ለመግታት ከእጅ ነቀላ ባለፈ የተለያዩ ሳይንሳዊ ዘዴዎችንም በዋነኛነት መጠቀም ይገባል ሲሉ ያስገነዝባሉ።

ሰው የሚማረው አንድም ከፊደል አንድም ከመከራ ነው፤ አንድም በሳር ‘ሀ’ ብሎ አንድም በአሳር ‘ዋ’ ብሎ ነው” ሲሉ ባለቅኔው ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን የተናገሩትን ጠቅሰው ፕሮፌሰሩ፣ ኢትዮጵያም እንቦጭ ካደረሰባት ጉዳት ለመላቀቅ በምርምር የተፈተሹ ሳይንሳዊ መንገዶችን ወደተግባር ማስገባት እንዳለባት ይመክራሉ።

ፕሮፌሰር ሽመልስ ሰሞኑን በኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ አዘጋጅነት በተሰናዳ መድረክ «እንቦጭና ሌሎች ወራሪ ዕፅዋት ለታዳሽ ኃይል እና የአካባቢ ጥበቃ ቴክኖሎጂዎች ያላቸው ፋይዳ፤ የኤሌክትሮ ኬሚስት ዕይታ» የተሰኘ ጥናታዊ ጽሁፍ አቅርበው እንቦጭን ወደ ኃይልነት በመቀየር



**ፕሮፌሰር ሽመልስ አድማሴ**



ጉዳቱን መቀነስ እንደሚቻል አስረድተዋል።

ተክሎችን ለተለያዩ የኃይል አማራጮች መጠቀም የሚቻልበት መንገድ እንዳለ ስዊድን አገር በተሳተፍኩባቸው የምርምር ስራዎች ዕውቀቱን አዳብሬያለሁ የሚሉት ፕሮፌሰሩ፣ የምርምር ልምዱን በመጠቀም እንቦጭን ለታዳሽ ኃይል መዋል የሚቻልበት መንገድ እንዳለ በጥናቴ አሳይቻለሁ ይላሉ።

ሃሳባቸውን ሲያስረዱም በአሁኑ ወቅት ከኮምፒዩተር ጋር የተገናኙ መጠቀሚያዎች፣ ስልክ፣ ሰዓት፣ እንዲሁም ለተለያዩ ኤሌክትሮኒክስ መገልገያዎች በኤሌክትሪክ አሊያም በፀሐይ ኃይል ቻርጅ የሚደረጉ ባትሪዎችን መያዛቸውን ይጠቅሳሉ።

እሳቸው እንደሚሉት፤ እነዚያ ባትሪዎች ደግሞ በውስጣቸው አካባቢን በሚበክሉና ዋጋቸው ውድ በሆኑ ንጥረ ነገሮች የተሞሉ ናቸው። በተለይ ክሮሚየም የተባለውን ንጥረ ነገር ተጠቅመው የሚዘጋጁ የስልክና የተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ መገልገያዎችን ለማንቀሳቀስ የሚረዳ የባትሪ ኃይል በሰው ልጅ ጤና ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንደሚያደርስ በሳይንስ ተረጋግጧል።

ክሮሚየም አካባቢን የሚበክል ከመሆኑ ባለፈ ካንሰርን የሚያስከትል ኬሚካል ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሰውን «ኤሌክትሮቫለንት ክሮሚየም» የተሰኘውን ኬሚካል ተጠቅመው ምርት የሚያዘጋጁ ፋብሪካዎች አሉ።

በሌላ በኩል ለኤሌክትሮኒክስ መገልገያዎች ኃይል የሚሰጡ ባትሪዎች ሊድ በተሰኘ ኬሚካል አማካኝነት ነው የሚሰሩት። ሊድ ደግሞ በቀላሉ ሊወገድ የሚችል ባለመሆኑ አካባቢን የመበከል ዕድሉ ከፍተኛ ነው። በተለይ ሊድ በአግባቡ ካልተወገደ የነርቭ ክፍሎችን በማጥቃት፣ የማየት ችሎታን በመቀነስና የተለያዩ የመተንፈሻ አካላት ላይ ጉዳት በማምጣት እንደሚታወቅ ፕሮፌሰር ሽመልስ ያስገነዝባሉ።

ለጤና ጎጂ የሆኑትን የባትሪ ኃይል ግብዓቶች ሊድ እና ክሮሚየምን አካባቢን በማይበክል ንጥረ ነገር ለመቀየር ደግሞ ተክሎች አማራጭ ሆነው በሰለጠነው ዓለም ጥቅም ላይ እየዋሉ እንደሚገኙ ይጠቁማሉ። ባትሪዎቹ አካባቢን የማይበክሉና ዋጋቸውም ተመጣጣኝ በሆነ ግብዓት እንዲዘጋጁ የደን ሀብቶችን ጥቅም ላይ ማዋል የሚቻልበት ሳይንሳዊ ምርምር በአውሮፓ፣ በአሜሪካና በእስያ ተግባራዊ ሆኗል ይላሉ።

ለአብነት ቻይና በቀርከሃ ምርት ትታወቃለች። የዓለምን ሁለት ሶስተኛ የቀርከሃ ምርት የምታዘጋጀውም ይህች ሀገር ናት። ቻይናዎች ቀርከሃን በተለየ መንገድ በላብራቶሪ ሂደት በማቃጠል የሚገኘውን ኬሚካል ለባትሪ ድንጋይ ምርት ግብዓትነት እየተጠቀሙ ነው።

በእኛ ሀገር ሁኔታ ደግሞ ጠቃሚ የሆኑትን ደኖች ለባትሪ ኃይል ግብዓት ከማዋል ይልቅ ጉዳት እያደረሱ የሚገኙ እንቦጭና በተለምዶ ወያኔ ዛፍ የተሰኙ አረሞችን ለዚህ አገልግሎት ማዋል ቢቻል የአረሞቹን ስርጭት በመቆጣጠር በተጓዳኝ ጥቅም ላይ ወደሚሰጥ ስራ መቀየር የሚያስችል ሁለት አላማ ይኖረዋል ሲሉ ያስረዳሉ።

በዚህ ረገድ እንቦጭ ተክል በኢትዮጵያ ለባትሪ ምርት ግብዓት የሚሆኑ የኬሚስትሪ ውጤቶችን በመተካት ረገድ የላብራቶሪ ምርምር ማድረጋቸውን ነው ፕሮፌሰር ሽመልስ የሚጠቁሙት።

ከሌሎች ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ካላቸው የደን ውጤቶች ላይ ለባትሪ መስሪያ የሚያገለግለውን ግብዓት ከምናወጣ /Extract/ ይልቅ የእንቦጭ ተክልን በመጠቀም አስፈላጊውን የባትሪ ማምረቻ ግብዓት ማግኘት እንችላለን በሚል በተካሄደ ምርምር አጥጋቢ ውጤት መገኘቱን ይጠቁማሉ።

እንደ ሌሎች ተክሎች ሁሉ እንቦጭ ውስጥ የሚገኘውን “ሊግኒን” የተሰኘውን ንጥረ ነገር በመጠቀም አካባቢን ሳይበክሉ መወገድ የሚችሉ የባትሪ ድንጋይ ግብዓቶችን ማምረት ይቻላል።

በላብራቶሪ ሂደት የእንቦጭ ተክልን ምንም አየር በሌለበት መንገድ በማቃጠል የሚፈለገውን የባትሪ ኃይል የሚሰጥ ካርበን ማግኘት ተችሏል። ይህን ግብዓት በአግባቡ መጠቀም የሚችል ኢንዱስትሪ በመገንባት ለሀገር የሚተርፍ ውጤት ማግኘት የሚቻልበት መንገድ አለ ሲሉ ተመራማሪው ያስረዳሉ።

እንቦጭን ማጥፋት ጊዜ የማይሰጠው ጉዳይ ነው። ስናጠፋው ደግሞ ለሌላ ጥቅም እያዋልነው ሲሆን የበለጠ አዋጭ ይሆናል። የሚሉት ፕሮፌሰሩ፣ ጣና ሐይቅን ጨምሮ በበርካታ የውሃ አካላት ብዝሀ ሕይወት ላይ ጉዳት እያደረሰ የሚገኘውን አረም ለማስወገድ ደግሞ የኬሚስትሪ ምርምሮች ወሳኝነት እንዳላቸው ይጠቁማሉ።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ በተደረጉ ጥናቶች በተለይ ከተለያዩ የመኪና ባትሪና የኤሌክትሮኒክስ ምርቶች ጋር ተያይዞ ጥቅም ላይ የዋለው ሊድ በተለያየ ባዮሎጂካል መንገድ ወደአፈር ውስጥ ብሎም ወደምንጠጣው ውሃ የመግባት ዕድል አለው። ይህ ሊድ በተለይ የህጻናትን የማሰብ ችሎታ የመቀነስና የማስታወስ ችሎታ የማዳከም እንዲሁም በአዋቂዎች ላይ የደም ግፊትና የተለያዩ የጤና ጉዳቶችን የማስከተል አቅም አለው።

በተጨማሪ ከእንቦጭ የሚገኙ የተለያዩ የኬሚካል ውጤቶች ደግሞ አካባቢን የማይበክል ባትሪ ለማዘጋጀት ከመዋላቸው ባለፈ በሊድ ኬሚካል አማካኝነት የተበከለ ውሃን ለማጣራት እንደሚረዱ ነው ፕሮፌሰር ሽመልስ የሚገልጹት።

ስለዚህ እንቦጭ ከጎጂ አረምነቱ ባለፈ በሳይንሳዊ ሙከራዎች ወደተለያዩ ጥቅም ሰጪ ግብዓቶች መቀየር እንደሚቻል በኬሚስትሪ ዘርፉ ምርምር ተደርጓል። ይህን የሳይንስ ምርምር ውጤት በስፋት ወደተግባር ለማዋል ደግሞ ከኢንዱስትሪዎችና ከተለያዩ ተቋማት ጋር ተቀራርቦ መስራት ያስፈልጋል። በዋናነት እንቦጭን ተጠቅሞ አካባቢን የማይበክልና በዋጋ ደረጃም አዋጭ የሆነ የባትሪ ኃይል ለማምረትና አረሙን ለተሻለ ውጤት ለመጠቀም የምርምር ውጤቱን የሚቀበሉ አምራቾች ያስፈልጋሉ።

በዚህ ረገድ የተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ ኃይል የሚሰጥ ባትሪም ሆነ የመኪና ባትሪ የሚያመርቱ ፋብሪካዎችና ግለሰቦች የምርምር ውጤቱን እንዲጠቀሙበት አስፈላጊውን ስራ በትብብር ለማከናወን ዝግጁ ነኝ ሲሉ ፕሮፌሰር ሽመልስ ይጠቁማሉ። በግልም ሆነ በተቋም ደረጃ የሚከናወኑ የሳይንስ ምርምር ውጤቶችን ወደ ተግባር በመቀየር ለአገር የሚጠቅም ስራ ላይ ማዋል ይገባል ሲሉም ነው ያስገነዘቡት።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በነፍሳት ሳይንስ ላይ ያተኮረው የኢንቶሞሎጂ ዘርፍ ተመራማሪ የሆኑት ፕሮፌሰር ኢማና ጌቱ በበኩላቸው፤ እንቦጭን በሳይንሳዊ ምርምር ለኃይል አማራጭ ግብዓትነት ለመጠቀም የተከናወነው ምርምር ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን ይጠቁማሉ።

ከዚህ ባለፈ ግን እርሳቸውና ጓደኞቻቸው በስምጥ ሸለቆ ውስጥ የሚገኙ መጤ አረሞችን ማጥፋት በሚቻልበት መንገድ ላይ ጥናት ማድረጋቸውንና በምርምራቸው በውሃማ አካላት ላይ የተንሰራፉ እንደ እንቦጭ ያሉ አረሞችን በሳይንሳዊ መንገድ ለማዳበሪያነት ማዋል የሚቻልበት አማራጭ መኖሩንም ማረጋገጣቸውን ያመለክታሉ።

ከዚህ ባለፈ እንቦጭን ለባዮ ኢታኖል ምርትና በላብራቶሪ ሂደት በማሳለፍ ተክሉ እንዲፈጭ ተደርጓል። ከዚህም የፕሮቲን መጠኑ ከፍተኛ የሆነ ንጥረ ነገር ስላለው፤ ለእንስሳት መኖነት ማዋል ይቻላል። በዚህና በተለያዩ መንገዶች አረሙን መቆጣጠር የሚቻልበት ሳይንሳዊ መንገዶችን ማዳበር ያስፈልጋል።

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ እንቦጭን ለኃይል አማራጭነት መጠቀም እንደሚቻል ያሳየውን ምርምር በስምጥ ሸለቆ አካባቢ እየተሰሩ ከሚገኙ ጥናቶች ጋር በማቀናጀት አረሙን ከማጥፋት ባለፈ ለተሻለ ጥቅም የሚውለበትን መንገድ ማመቻቸት ይገባል።

የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዝዳንት ፕሮፌሰር ያለምፀሐይ መኮንን በበኩላቸው፤ ብዝሀ ሕይወት ላይ ጉዳት እያደረሱ በሚገኙ እንደ እንቦጭ ያሉ መጤ አረሞች ላይ የተደረጉ ሳይንሳዊ ምርምሮችን መጠቀም የሚጠበቅብን ጊዜ ላይ ነን ሲሉ አመልክተው፣ በዚህ ረገድ ስለሀገሩ የሚያስብ ጆሮ ያለው ሁሉ ሊሰማ ይገባል ይላሉ።

ሳይንሱን በአግባቡ ከተጠቀምንበት ከአገር ግንባታ፣ ከጤናና ከአካባቢ ጥበቃ ረገድ ውጤት ማግኘት ይቻላል። ለዚህም ተመራማሪዎችን በመደገፍና የላብራቶሪ ጥናታቸውን በአገር አቀፍ ደረጃ እንዲተጉበሩት ማድረግ ያስፈልጋል።

እንደ ፕሮፌሰሯ ገለጻ፤ ሳይንሳዊ ግኝቱ አረሙን ለመጠቀም ብቻ ሳይሆን አሁን ላይ እየተመረቱ ያሉ ለጤና ጎጂ የሆኑ የባትሪ ግብዓቶችን ለመተካት የሚረዳ ዘርፈ ብዙ ጥቅም ያለው ምርምር ነው። ሳይንሳዊ ግኝቱ ተፈላጊውን መፍትሄ እንዲያመጣ ምርምሩን አጠናክሮ መቀጠልና በአገር አቀፍ ደረጃ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የዩኒቨርሲቲዎች «ራስ ገዝ»መሆን ያለው ፋይዳ

**ክብረአብ በላቸው**

ትምህርት ሚኒስቴር በሚቀጥሉት ሶስት ወይም አራት ዓመት ጊዜ ውስጥ አስር የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎችን ራስ ገዝ ለማድረግ እቅድ ይዟል። በዚህ እቅድ ውስጥ ከተካተቱት ውስጥ፤ የባህርዳር፣ ጎንደር፣ ጅማ፣ ሀዋሳ፣ አርባ ምንጭ እና ሀሮማያ ዩኒቨርሲቲዎች ይገኙበታል። አንጋፋው እና ከተቋቋመ ከሰባ ዓመታት በላይ ዕድሜ ያስቆጠረው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የዚሁ ዕቅድ አካል ሆኖ የ"ራስ ገዝ" አስተዳደርን ተግባራዊ በማድረግ የመጀመሪያው ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል።

የዩኒቨርሲቲዎች "ራስ ገዝ" መሆን፤ የአካዳሚ፣ የአስተዳደር፣ የፋይናንስ እና የሰው ሀብት አስተዳደራቸው ላይ ነጻነት እንዲኖራቸው እንደሚያደርግ የትምህርት ሚኒስቴር በተለያዩ ጊዜያት ሲገልጽ ቆይቷል። አስተዳደራዊ ነጻነቱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ የራሳቸውን አደረጃጀት እና መዋቅር የመዘርጋት ስልጣን እንደሚሰጣቸው በማንሳት፤ በዚህ መሰረት ዩኒቨርሲቲዎቹ ከፍተኛ አመራሮቻቸውን ጨምሮ በመዋቅራቸው ውስጥ የሚያስፈልጓቸውን የአመራር እና የአስተዳደር አካላትን በራሳቸው መመደብ እንደሚያስችላቸው ጭምር ተጠቅሷል።

እንዲሁም ለትምህርት ጥራት፣ በተቋማቱ መካከል የትብብር እና የፉክክር መንፈስ በማምጣት ልሕቀትን ለማረጋገጥ እንደሚያግዝ ነው የተገለጸው። አጠቃላይ ድምር ውጤቱም በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲን ዕውን ለማድረግ እንደሚረዳ ታምኖበታል።

ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ የኢትዮጵያ ፌዴራለዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሚንስትሮች ምክር ቤት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ነጻ ሆነው ስለአካዳሚክ ስራዎቻቸው በራሳቸው መወሰን እንዲችሉ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የመማር ማስተማር እና የምርምር ሥራ የዳበረ ዕውቀት የሚገኝባቸው እንዲሆኑ፤ ሕብረተሰቡ ዘርፈ ብዙ የማህበራዊ አገልግሎቶችን የሚያገኝባቸው፤ የራሳቸውን የገቢ ምንጮች በማስፋት በሂደትም በራሳቸው በጀት የሚተዳደሩ እንዲሆኑ ማስቻልን ታሳቢ ያደረገ ነው። ቀስ በቀስ በመንግስት ዩኒቨርሲቲዎች ላይ የሚተገበር ረቂቅ አዋጅ ለሚንስትሮች ምክር ቤት ቀርቧል። ምክር ቤቱም ግብዓቶችን በማከል ይጸድቅ ዘንድ ወደ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከሁለት የዩኒቨርሲቲ አመራሮች ጋር ቆይታ አድርጓል። የሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ጀማል ዩሱፍ እንደሚናገሩት፤ ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ ሲሆኑ ፋይዳው በተለይ ጥራት ያለው ምርምር ለማከናወን እንዲሁም ጥራት ያለው ትምህርት ለመስጠትና ብቁ ተማሪ ለማስመረቅ ዩኒቨርሲቲዎች አሰራራቸውን በራሳቸው መወሰናቸው ትልቅ እምርታ ነው። እንደ ምሳሌ ሲያነሱም ዩኒቨርሲቲዎች ምን አይነት አቅም ያለው ተማሪ ነው ተቀብለን አስተምረን የምናበቀው፣ የሀገራችን የትኩረት አቅጣጫ እንዳለ ሆኖ በምን አይነት የትምህርት መስክ የሚለውን ሁሉ በራስ መወሰን መቻል አንድምታው ብዙ ነው ይላሉ። ከእነማን ጋር አጋር ሆነን ምን አይነት ምርምር እንስራ የሚለውን ለመወሰንም አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። ለአብነት አውሮፓ እና አሜሪካ ከሚገኙ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመተባበር በጣም ፕሮግሬስቭ የሆኑ የትብብር ምርምሮች አሉ፤ እነኚህን እና መሰል ስራዎችን በተገቢው መልኩ ለመስራት ራስ ገዝ የመሆኑ ሁኔታ ስራዎችን የሚያፈጥንልን ነው የሚሆነው ብለዋል።

የዩኒቨርሲቲው ራስ ገዝ መሆኑ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነቱን እንደሚያሳድገው የተነገሩት ዶክተር ጀማል በዚህ ረገድ የሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ የከፍተኛ ትምህርት ተቋሟት ራስ ገዝ እንዲሆኑ የተጀመረውን ጥረት ታሳቢ በማድረግ የራሱን ዝግጅት እያከናወነ ይገኛል። በዚህም እንደ የዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ሥራ ያደረግነው ራስ ገዝ የመሆን ሀሳቡን ዩኒቨርሲቲ



ዶክተር ጀማል ዩሱፍ



ዶክተር ዘውዱ እምሩ

**ዩኒቨርሲቲዎች መንግስት ከፍቷቸው ስማቸውን ብቻ ይዘው የመቀጠል ብቻ ሳይሆን የመኖር እና ያለመኖር ጉዳያቸው ዛሬ ላይ በሚያደርጓቸው መልካም ተግባራት የሚወሰን ይሆናሉ**

ማህበረሰብ ማስገንዘብ ነው። በዚህ ረገድ የተለያዩ የውይይት መድረኮችና ዝግጅቶች ተካሂደዋል፤ በራስ ገዝነት አስተዳደር ዙሪያ የአዕምሮ ዝግጁነት እንዲመጣ በተለያዩ መድረኮች ላይ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራዎች ሲሰሩ ቆይቷል። በተለይም ሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ ከምሥረታው ጀምሮ ከውጭ ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ግንኙነት የነበረው በመሆኑ የውጭ አገር ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ ሲሆኑ እንዴት ሀብት ማሰባሰብ እንደቻሉና በምን መልኩ ሥርዓቱን ማስኬድ እንደቻሉ ለማወቅ የተለያዩ ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል።

ዶክተር ጀማል እንደሚናገሩት፤ ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲውን መርጠው መምጣት እንዲችሉ ዩኒቨርሲቲው ያለውን የሰው አቅም በመገንባት፣ አስፈላጊ ግብዓቶችንም በማሟላትና በቴክኖሎጂ የታገዘ የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል የሚያስችል ሥራ በመሥራት ላይ ነው። ከዚህ ባለፈ በተጓዳኝ አገልግሎቶች የዩኒቨርሲቲውን የፋይናንስ አቅም የማጠናከር ሀብት የማመንጨት ሥራ ላይ ትኩረት አድርጎ እየሰራ ነው።

በዚህ ረገድ በእጃችን ያሉ ፈስሊቲዎች አሉ፤ በግብርና በተለይ በስንዴ ዘር አቅርቦት፣ በሕክምና እና በተለያዩ ሴክተሮች ላይ ሀብት ለማመንጨት ታሳቢ ተደርጎ እየተሠራ ነው። የገቢ ምንጭን ከማስፋት አንጻር ዩኒቨርሲቲው ያለውን የእርሻ ሀብቶችን በመጠቀም ምርቶችን በማሰባሰብ፣ ምርጥ ዘርን በማዘጋጀትና ተደራሽ በማድረግ፣ የዩኒቨርሲቲውን የማስተማሪያ ሆስፒታል የሕክምና ቱሪዝም ማዕከል በማድረግ ተጨማሪ ገቢ ለመፍጠር የሚያስችል ዕድል አለው።

የሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ የምርምር ዩኒቨርሲቲ እንደመሆኑ መጠን ከሥራው ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ባለው አግባብ የራስ ገዝ ሆኖ መሥራት እንዲችል የሚረዳ ግብረ ኃይል ተቋቁሞ እየተሠራ መሆኑን የገለፁት ዶክተር ጀማል፤ ዩኒቨርሲቲው በእራሱ የንግድ ድርጅት አማካኝነት ገቢ ማመንጨት የሚያስችለው መመሪያ ተዘጋጅቷል፤ የተዘጋጀው መመሪያ በዩኒቨርሲቲው ቦርዱ ከጸደቀ በኋላ እንደማንኛውም የንግድ ድርጅት ራሱን ችሎ መዋዕለ ነዋዮችን በማንቀሳቀስ፣ ሀብት እንዲያመነጭ የሚያስችል ሁኔታ ይመቻቻል ብለዋል።

የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ የኢንፎርሜሽን እና እስትራቴጂክ ኮሙዩኒኬሽን ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ዘውዱ እምሩ በበኩላቸው፤ የዩኒቨርሲቲ ራስ ገዝ መሆን በራሱ ምን ማለት ነው የሚለውን ሲያብራሩ፤ ከዚህ በፊት በሀገር አቀፍ ደረጃ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚተዳደሩት ሙሉ በሙሉ በመንግስት እና በሲቪል ሰርቪስ ስር ነው የሚተዳደሩት እንደማንኛውም የሲቪል ሰርቪስ ስር እንዳለ ተቋም ነው። በራሳቸው ነጻነት የላቸውም። በበጀት፣ ባለሙያ ቅጥር፣ በመሳሰሉት የሲቪል ሰርቪስን ህግ ተከትለው ብቻ ነው የሚንቀሳቀሱት፤ ይሄ ደግሞ በብዙ መልኩ አሳሪ ነው። የዩኒቨርሲቲ ነጻነትን ይገድባል። ለትምህርት ጥራትም የራሱ የሆነ ውስንነት እንዲኖር ያደርጋል።

አዲሱ አሰራር ግን እነዚህን ጉዳዮች በመቀያየር መንግስት የሚያደርጋቸው የበጀት እና ሌሎች ድጋፎች እንዳሉ ሆነው፤ የራሱን የዩኒቨርሲቲ አስተዳደር ነጻነትን ያጎናጽፋል። ያም ሆኖ ግን የመንግስት በጀት እስከ ወዲያኛው ይቀጥላል ማለት አይደለም። በየዓመቱ እንደ አፈፃፀማቸው እየታየ በየጊዜው እየተቀነሰ በሚሄድ ደረጃ በጀት አሁንም ከመንግስት የሚመደብላቸው ሆኖ የውስጥ አሰራራቸውን ማለትም የሰራተኛ ቅጥር፣ የደመወዝ ጉዳይ እና መሰል አሰራሮችን ለማዘመን ከግዥ ጋር በተገናኘ ያሉትን በጣም ጊዜ የሚወስዱ ጉዳዮችን ለማሳጠር የሚያስችሉባቸው የራሳቸው የሆነ አካሄድ እንዲመሰርቱ የሚያበረታታ አሰራር መሆኑን ይናገራሉ።

ዶክተር ዘውዱ ሲያስረዱ ዩኒቨርሲቲዎች ሙሉ በሙሉ በመንግስት በሚተዳደሩበት ጊዜ መንግስት እንደሚመድበው በጀት ተማሪዎችንም ይመድባል። በአጠቃላይ ከላይ ወደ ታች የሚመጡ ነገሮች ይበዛሉ። አሁን በራስ ገዝ መተዳደር ሲጀምሩ ግን ከመጀመሪያው ዩኒቨርሲቲዎች የሚያስተምሩትን ተማሪ በራሳቸው ይመርጣሉ፤ ይመጥናሉ ለዚህም ሁኔታዎችን ማመቻቸት አለባቸው። ይህ ብቻ አይደለም መምህራንም ሆነ ሌሎች የአስተዳደር ሰራተኞችም ቢሆን ይሄ "ጥሩ ቦታ ነው" ብለው ዩኒቨርሲቲውን መርጠው እንዲመጡ ዩኒቨርሲቲዎች መስራት እና በሌሎችም ተመራጭ መሆን አለባቸው። ይህ የሚሆነው ደግሞ መጀመሪያ የትምህርት ጥራታቸው ሲያድግ ነው። ስለዚህ የትምህርት ጥራታቸው፣ የካሪኩለም፣ የመማር ማስተማሩ፣ የምርምር፣ አጠቃላይ የማኔጅመንት ጉዳዮች ሁሉ ከነበረበት ደረጃ ከፍ ያለ ሆኖ ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ተወዳድሮ ገበያ ላይ ተመራጭ ሆኖ መገኘት ይጠበቅባቸዋል። በዚህ ረገድ የራስ ገዝ ስርዓቱ የሚያመጣው አንዱ ጥቅም ዩኒቨርሲቲዎች አሁን ካሉበት አቅም የተሻለ ተመራጭነትን ለማምጣት የበለጠ እንዲሰሩ ያደርጋል። የትምህርት ጥራትን ተግባራዊ ማድረግ የሚጀምሩበት ሁኔታ ይፈጠራል ይላሉ።

ከዚህ በተጨማሪ የውስጥ የሰው ኃይል (ነባሩም ሆነ አዲስ) የሚመጣው ሰራተኛ አቅሙን በማሳደግ ለሙያዊ እድገት ለመልካም ነገር ሁሉ የሚተጋበት ስርዓት ይፈጠራል። ስለዚህ ዩኒቨርሲቲዎች መንግስት ከፍቷቸው ስማቸውን ብቻ ይዘው የመቀጠል ብቻ ሳይሆን የመኖር እና ያለመኖር ጉዳያቸው ዛሬ ላይ በሚያደርጓቸው መልካም ተግባራት የሚወሰን ይሆናሉ ማለት ነው።

ስለዚህ እነዚህ ሁሉ ነገሮች አንድ ላይ ተጠራቅመው ሲታዩ አወንታዊ የሆነ ፉክክር እርስ በእርሳቸው ላይ ይፈጥር እና በጣም ላቅ ያለ አቅም ያላቸው ሆነው በአገር አቀፍ፣ በአህጉርም ይሁን በዓለም አቀፍ ደረጃ የተሻለ ተወዳዳሪ የሆኑ ተቋማት ኢትዮጵያ ማግኘት እንደምትጀምር ያላቸውን እምነት ይገልጻሉ።

እንደ ዶክተር ዘውዱ ገለጻ፤ አንድ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም በዚህ ደረጃ ተወዳዳሪነቱ እየጨመረ ሄደ ማለት እንደ ሀገር ፋይዳው ከፍተኛ ነው። ስለዚህ ጥራት ያለው ምርምር ይሰራል ማለት ደግሞ በሀገራችን ውስጥ ላሉ ውጥንቅጦች ሁሉ መልስ ሊሰጡ የሚችሉ ምርምሮች ይሰራሉ ማለት ነው። ይህ በሌላ ቋንቋ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ለሀገሪቱ እድገት የሚጠበቅባቸውን ሚና በመጫወት ለችግሮች መፍትሔ ሰጭ ሆነው መቆም ይችላሉ የሚል መረዳት ነው ያለው።

በዚህ ረገድ የባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ዝግጅት ምን እንደሚመስል ያነሱት ዶክተር ዘውዱ፤ የባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ነባር እና የውጭ ሀገር ልምድ ያላቸው ፕሮፌሰሮች ያሉበት አንድ የዩኒቨርሲቲ ራስ ገዝ የዝግጅት ቡድን አቋቁሞ እየሰራ ነው። የዚህ ቡድን ኃላፊነት በሀገር ውስጥም በውጭ ሀገርም ከዚህ ጋር ተያይዞ ያሉትን ልምዶች በማጥናት ሌሎች የውጭ ሀገር ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝነትን ለማምጣት ምን ሲያደርጉ ቆዩ ? የትኞቹ ተግዳሮት ገጠመቸው? የትኞቹ የተሳካ ሂደት ነበራቸው በሚል በርካታ ጥናቶችን እያጠኑ ለዩኒቨርሲቲው ማሕበረሰብ የማስገንዘብ ስራ ተሰርቷል። ከዚህ በተጨማሪ ባሳለፍነው ሳምንት የትምህርት ሚንስቴር ሚንስትር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋን ጨምሮ የትምህርት ሚንስቴር ከፍተኛ ኃላፊዎች በተገኙበት ሰፊ ውይይት ተደርጓል። አሰራሩን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል መደላድል ለመፍጠር እየተሰራ መሆኑንም አንስተዋል ዶክተር ዘውዱ።

ምሁራኑ እንደስጋት ያነሱት፤ የዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ መሆን አዲስ አሰራር በመሆኑ ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ። ነገር ግን ይህ አሰራር በቀጣይ ካለው ሀገራዊ ጠቀሜታ አንፃር ሊያገጥሙ ለሚችሉ ተግዳሮቶች የመፍትሔ ሀሳቦችን በማፍለቅ መስራት ይጠበቃል ብለዋል። ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ መሆናቸው በውድድር መንፈስ በመስራት ውጤታማ እንዲሆኑ የሚያስችል በመሆኑ በትኩረት መስራት ከሁሉም ባለድርሻ አካላት እንደሚጠበቅ አጽንኦት ሰጥተው ተናግረዋል።

ሁለቱም ምሁራን እንደሚስማሙበት፤ የዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ መሆን የተለያዩ ጠቀሜታዎች ቢኖሩትም፤ ከሁለም በላይ ግን ለትምህርት ጥራት የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ጉልህ ነው። ችግር ፈቺ ምርምሮችን በማድረግም ሀገራዊ ችግሮችን የመፍታት ፋይዳው ጉልህ መሆኑን ይናገራሉ። በዩኒቨርሲቲዎች መካከል የውድድር መንፈስን መፍጠርና ጠንካራ ዩኒቨርሲቲዎች እንዲኖር ማድረግ በራሱ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ያስረዳሉ።

ማህበራዊ

# ሴቶች

## «መኪና ማስዋብ ራሱን የቻለ አርት ነው»

- ወይዘሮ ኢክራም እድሪስ
የኢክራም ሞተር ማኑፋክቸሪንግ ትሬዲንግ ማህበር መሥራችና ባለቤት

ሰላማዊት ውቤ




ስኬታማዎቹ ሴቶች
ፎቶ፡- ፀሐይ ንጉሤ

የኢክራም ሞተር ማኑፋክቸሪንግ ትሬዲንግ ማህበር መሥራችና ባለቤት ናቸው፡፡ ወይዘሮ ኢክራም እድሪስ፡፡ ይሄን በስፋት በወንዶች የተያዘ ዘርፍ እሳቸው በዘመናዊ መልኩ በቴክኖሎጂ በተደገፈ ማሽን ይስሩት እንጂ እናታቸውም በባህላዊ አሰራር ተሰማርተውበት ለረዥም ጊዜ ይዘውት ቆይተዋል፡፡ ለወላጆቻቸው ሁለተኛ ልጅ የሆኑት ኢክራም ተወልደው ያደጉት ደሴ ከተማ ውስጥ ነው፡፡የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በደሴ ከተማ፤ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ደግሞ ሻሸመኔ በሚገኘው ኩየራ አዳሪ ትምህርት ቤት ነው የተማሩት፡፡ አባታቸው ገና በህፃንነታቸው በመኪና አደጋ በመሞታቸው በእናታቸው እጅ ነው ያደጉት፡፡ ከእናታቸው ጋር አብረው ይኖሩ የነበሩት ሴት አያታቸውም በእድገታቸውና በዛሬ ማንነታቸው ቀረፃ ላይ ከወላጅ እናታቸው ያልተናነሰ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ራሳቸው ይናገራሉ፡፡ እንዲያውም ሕብረተሰቡ ለወንድ በሰጠው የጋራዥ ሥራቸው ፀባይ ምክንያት እናታቸው እጃቸው በግራሶ እየተጨማለቀ መኪና ሲገጥሙና ሲፈቱ እንዲሁም ሲያሰማሩና ሲያስጭኑ ውጭ ውጭውን ስለሚሉ እሳቸውን ጨምሮ እህትና ወንድሞቻቸውን ያሳደጓቸው አያታቸው ነበሩ።

ሥራን በፍጥነት ማከናወን ባህላቸው ነው፡፡ አነጋገራቸውም ቢሆን እንደ እርምጃቸውና ሥራቸው ፈጠን ፈጠን ያለ ነው፡፡ ፈጣን አረማመዳቸው አዘወትረው ከሚለብሱትና ለሥራና ለእንቅስቃሴ ምቹ ነው ከሚሉት ጃኬትና ሱሪ ጋር ተዳምሮ ወንዳ ወንድ ያስመስላቸዋል፡፡ ድምፃቸውም ወፈር ጎርነንና ቆጣ ያለ ነው፡፡ በተፈጥሮ ከተሰጠው ውጭ በወንድና ሴት መካከል ባለው በየትኛውም ልዩነት አያምኑም፡፡ ቢሆንም ይሄ እምነታቸውም ሆነ ባህርያቸው ሴትነትን በመጥላት ወንድ ለመምሰል ሆን ብለው ያደረጉት አይደለም፡፡ ገና የአንደኛ ደረጃ ተማሪ ሳሉ የፍቅር ጥያቄዬን አልተቀበልሽም ብሎ ሊያስፈራራቸው የሞከረ ወንድ ተማሪን "በዚህ ሰዓት እዚህ ጋር ጠብቀኝና ይዋጣልን" የሚል ደብዳቤ እንዲደርሰው ካደረጉ በኋላ በሚገጥሙት ጊዜ በውስጣቸው እየተገነባ የመጣ የእኩልነት ማረጋገጫ ነፀብራቅ ተፈጥሮ ነው። በጭንቅላታቸው ላይ የሚጠመጥሙት ሻሽም ውቡንና ሴታ ሴት የፊት ገጽታቸውን ስላደበዘዘው ሴትነታቸውን መለየት የሚቻለው ሲቀርቧቸው ነው። በተለይ ካምፓኒያቸው ውስጥ ቱታቸውን በመልበስ መኪና ሲፈቱና ሲገጣጥሙ ያዩ ሴትነታቸውን ፈጽሞ አይጠረጥርም፡፡ ሥራው በስፋት በወንዶች ሲሰራ መኖሩና መለመዱ ደግሞ ወንድ እንጂ ሴት ወዳለመሆናቸው ድምዳሜ ላይ ከማድረሱም በላይ ለየት ያሉ የሚያስመስላቸው አትኩሮት ያስቸራቸዋል።"እንዴት ሴት እንዲህ ዓይነቱን ከባድ የጉልበት ሥራ ትሰራለች?" ብሎ ራስን ለመጠየቅም ያስገድዳል። በዓለም የሚገኙ ታዋቂ ስም (ብራንድ) ያላቸውን መኪኖች የአካል ክፍሎቻቸውን ዓይነት ስም በየአገራቱ ቋንቋዎች ሲዘረዝሩ ላያቸው በአግራሞት ፍዝዝ ያደርጉና በአድናቆት ያስደምማሉ፡፡"እንደዚች ዓይነቷ ሴት ለታዳጊና ለወጣት ሴቶች አርአያ ያልሆነች ማን ሊሆን ነው?" በሚል ነበር ባለፈው ሳምንት የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ኢክራም የሥራ ተሞክሯቸውን እንዲያካፍሉ ያደረገው።

ምክር ቤቱ የዘንድሮ የዓለም የሴቶች ቀንን አስመልክቶ የራሳቸውን የገቢ ማስገኛ ሥራ በመፍጠር ከስኬት ደረጃ የደረሱ ሴቶችን አስተዋውቋል፡፡ የእውቅና እና የማበረታቻ ሽልማት ሰጥቷል፡፡ "የሴቶች የቢዝነስ አመራር" በሚል በኢንተር ላግዠሪ ሆቴል ባዘጋጀው የፓናል ውይይት ኢክራምን ጨምሮ የሕክምና ክሊኒክ ፈር ቀዳጅና የአከርካሪ አጥንት ሐኪም ዶክተር ሰላም አክሊሉ እንዲሁም አሁን ላይ በመላው አገሪቱ 40 ቅርንጫፎች ያሉት የካልዲስ ኮፊ ዘመናዊ ካፍቴሪያ መስራችና ባለቤት ወይዘሮ ፀደይ አስራት ታድመዋል። በተጨማሪም የውዳሴ ግሩፕ መሥራችና ባለቤት ወይዘሮ ውዳሴ እንቁስላሴን በድምሩ አራት ስኬታማ ሴቶችን በመጋበዝ የጠንካራ ሥራ ባህል ተሞክሯቸውን በሴትነት ከገጠማቸው ውጣ ውረዱ ጋር እያዋዙ ለታዳሚው እንዲያካፍሉ አድርጎ ነበር፡፡ በአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የ75 ዓመት ታሪክ የመጀመሪያዋ ሴት ፕሬዝዳንት በመሆናቸው ከስኬት ደረጃ ከደረሱት የሚሰለፉት የምክር ቤቱ ፕሬዝዳንት ወይዘሮ መሰንበት ሸንቁጤ ሁሉም ተሞክሯቸውን እንዲያቀርቡ በተጋበዙት መሰረት ወይዘሮ ኢክራምም በመድረኩ ተሞክሯቸውን አቅርበዋል፡፡ እኛም ለዛሬ የኢክራምን ተሞክሮ ልናጋራችሁ ወድደናል፡፡

በስፋት ወንዶች ወደ ተሰማሩበት መኪና የማስዋብና የጋራዥ ዘርፉን ወደ ማዘመን ዘርፍ ሲገቡ ዓላማ አድርገውት የነበረው የቆሸሸውን የጋራዥ ሥራ አካባቢ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝ ፅዱ ማድረግም ጭምር ነበር፡፡ "ቀደም ብዬ በሥራው ስላለፍኩ የጋራዥ ሥራ አካባቢን እውቀዋለሁ"የሚሉት ኢክራም እንዳከሉት ልኩስኩስና ዝርክርክ ነው።

ሂደቱም፣ ቅልጥፍና፣ ፍጥነትና ጥራት አልነበረውም፡፡ የፍሬን ዘይትና ግራሶ ልብስና እጅ ያጨማልቅና ያቆሽሻል፡፡ ከዚህ ዓይነቱ ባህላዊ አሰራር መውጣት፣ ሥራውንም በደርዝ በደርዙ በመከፋፈል መለየት አስፈላጊ እንደሆነ ያምኑ ነበር፡፡ ይሄንኑ ሀሳብ ሰንቀው ወደ ዘርፉ ሲገቡ ከእናታቸው የቀሰሙት ልምድና የአስተዳደር ጥበብ መደላድል ስለሆነላቸው አልተቸገሩም፡፡ ምንም እንኳን ለወላጆቻቸው ሁለተኛ ልጅ ቢሆኑም እንደ አብዛኞቹ ኢትዮጵያን ሴት ልጆች በማንኛውም የቤት ውስጥ የሥራ ጫና አላለፉም። እናታቸው ይልቁኑም ሙሉ በሙሉ ትኩረታቸው ትምህርት ላይ እንዲሆን ስለሚፈልጉም ነበር ኩየራ አዳሪ ትምህርት ቤት ያስገቧቸው፡፡ ሆኖም ለእረፍት በሚመጡበትና በሥራቸው ፀባይ ምክንያት ቤት ውስጥ በማያገኙዋቸውና ለማግኘት ወደ ሥራ ቦታቸው በሚሄዱበት ጊዜ ልክ እንደ ዶሮ ብልት ሁሉ እያንዳንዱን የመኪና አካል ክፍል ደህና አድርገው ያስጠኗቸው ነበር፡፡ እሳቸው በፊናቸው ልጆቻቸው በዚህ መልኩ ጥርሳቸውን ነቅለው እንዲያድጉ ማድረጋቸውን የሚያወሱት ኢክራም እናታቸው በተለይ ትምህርት ቤት ተዘግቶ ረዘም ላለ የክረምት እረፍት ወደ ቤት መጥተው ወደ ሥራ ቦታቸው በሚሄዱበት ጊዜ ስለ መኪና እና አጠቃላይ ጋራዥ ሥራ እንዲለማመዱ አድርገው ያሰደጓቸው መሆኑን ያስታውሳሉ፡፡

ከመኪና አካል ፈትቶ መገጣጠም ጀምሮ በቅጥቀጣው ረገድ ባሉት የሥራ ሂደቶች ሁሉ ያኔ ገና ነው የተካኑት፡፡ ሁኔታው ራሳቸውን ችለው በዘርፉ በሚሰማሩበት ጊዜ ከባዱን ሥራ አቅሎላቸዋል። ሆኖም ብዙ በመጓዝ ያሰቡበት ዘርፉን የማዘመን ስኬት ማማ ላይ ሳይወጡ ትዳር ውስጥ ገቡ፡፡ "ትዳር መሥርቼ ልጆች በመውለድ ሳሳድግ ከቆየሁ ከ10 ዓመት በኋላ ነው የተመለስኩት" ይላሉ፡፡ ታዲያ እሳቸው ስኬቴ የሚሏቸው በዚህ መልኩ ዋጋ የከፈሉላቸው ልጆቻቸውና ቤተሰባቸው ጭምር ናቸው፡፡ ዋጋ መክፈሉ በሕብረተሰቡ ውስጥ ከግምት ባይገባም እንደ ሴትና እናት ትልቅ ቦታ የሚሰጠው የተለመደ ተግባር ነው፡፡ አገርን የሚመሩ ሰዎች የሚያዘጋጁና የሚያቀርቡትም ሴቶች ከመሆናቸው አንፃር ትዳር መመሥረታቸው ልጆች ወልደው በማሳደግ እስከ 10 ዓመት ሥራውን በይደር ማቆየታቸው ኢክራም ለግል ቤተሰብ ብቻ ሳይሆን ለሕብረተሰብና ለሀገር ሲባልም የሚደረግ በመሆኑ ያምናሉ፡፡ እንደማይቆጨበትም ይናገራሉ፡፡ "ቁም ነገሩ ከዚህ ሁሉ ዓመታት በኋላ መመለሴና ያሰብኩበት መድረሴ ነው" ይላሉ።በእርግጥ ኢክራም አሁን ላይ በወንዶች በተያዘ የሥራ ዘርፍ ሴቶች መሰማራት እንደሚችሉና ውጤታማም እንደሚሆኑ ስኬታማ በሆነ ተግባራቸው አሳይተዋል። ያሳዩት እንዲህ በቀላሉ አይደለም። ከጋራዡ ዘርፍ ጋር ከእናታቸው ያገኙት ባህላዊ አሰራር ልምድ እንደተጠበቀ ሆኖ ሥራውን በዘመናዊ መንገድ ለመሥራት ልጆቻቸውን ከማሳደጉ ጎን ለጎን በግላቸው ራሳቸውን በተለያየ መንገድ ሲያስተምሩ በመቆየታቸው ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ደግሞ ‹‹በዘርፉም ቢሆን የባከነ ጊዜ የለኝም ማለት እችላለሁ›› የሚሉት ኢክራም የተለያዩ የአገር ውስጥና የውጭ ስልጠናዎችን ሲወስዱ በመቆየት ወደ ዘርፉ መግባታቸውን ይናገራሉ፡፡ በመሰልጠንና በማሰልጠን እንዲሁም ከውጭ ዕቃዎችን በማስመጣት በባለቤታቸው የመኪና ዕቃ መለዋወጫ ውስጥ ተመድበው መሥራታቸውም ጥሩ ልምድ እንዲያገኙ አግዟቸዋል። ዓለም ላይ ቁጥር አንድ ኢንዱስትሪ የሚባለው ሰፊ ገበያ የሚከናወንበት ዘርፍ ይሄ የአውቶሞቲቭ ዘርፍ እንደሆነም ያነሳሉ፡፡ በመሆኑም ከፊላንድና ከተለያዩ የውጭ አገራት ለሥራቸው ግብዓት የሚሆኑ ምርቶችን እንደሚያመጡም ያወሳሉ። በዚህ መልኩ እንዳሰቡት የጋራዥ ዘርፉን ማዘመን ችለዋል። የጋራዡ ሥራ በቴክኖሎጂ በመታገዙ በፍጥነት መከናወን እንዲሁም ጥራቱ መጠበቅ ችሏል። ሥራው የሚከናወንበት ሥፍራ ገጽታው በራሱ ወደ ጽዱና ውብነት ለመቀየር በቅቷል፡፡ ‹‹መኪና ማስዋብ ራሱን የቻለ አርት ነው›› የሚሉት ወይዘሮ ኢክራም ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ የተሰየመለት የራሱ ዘመናዊ ሂደት እንዳለውም ያብራራሉ፡፡ ተግባሩ መኪናን በቀለም ማስዋብንም እንደሚጨምርም ያወሳሉ።ሥራው በቅብብል የሚሰራ ሲሆን ቅብብሉ አካሉ (ቦዲው) ከአንዱ ወደ ሌላው ቦታ ከተሸጋገር በኋላ ተመልሶ ለሌላ ሥራ እዛው የሥራ ሂደት ላይ የሚመጣበት አጋጣሚ አለ፡፡ ለአብነት የመኪና አካል ከአቧራ ነፃ እንዲሆን ማድረግ የሥራው የመጀመሪያ ክፍል ነው፡፡ ከዛ ደግሞ ጓንት ተደርጎ በእርጥቡ ኬሚካል በእጅ ይታሻል፡፡ ይፈገፈጋል፡፡ ከዛ ላሜራ ይደረጋል (ይቀጠቀጣል) ይሄን የሚሰራ የራሱ የሥራ ሂደት ሲኖረው ላሜራ ተሰርቶ ተመልሶ በመምጣት ይረጋግጣል፡፡ ኢክራም ከቻክ በኋላ ያለውን የጋራዥ ሥራ ነው በተለየ ሁኔታ በቴክኖሎጂ በማዘመን ወደ ገበያ በመግባት በማሽን የሚሰሩት፡፡ እዚህ ታዲያ አካሉ (ቦዲው) ተገጣጥሞ ቀለም በሚቀባበት ጊዜ ብዙ ችግሮች አሉ፡፡ ቀለም ተቀብቶ መልሶ ሲመጣ ፊሽ አይስ ተብሎ ከሚጠራውና ቀለም ከሚያነባው ጀምሮ ብዙ ችግሮች ስላሉ እነዚህን ችግሮች በቴክኖሎጂ በመታገዝ ይፈታሉ፡፡ ከብዙ የሥራ ሂደቶች በኋላም በውበት የደመቀና የተንቆጠቆጠ የገጽታ ለውጥ ይመጣል።ይሄ በባህላዊ አሰራር ተልኮስኩሶ በኖረው በጋራዥ ሥራ ሥፍራውም ቀድሞ እንዲጸዳ የተደረገ በመሆኑ በእጅጉ ለዓይን ይማርካል፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜ የመኪና አካል የመግጠም ሥራን ከባህላዊ አሰራር ወደ ዘመናዊ በማሸጋገር ሙሉ በሙሉ በማሽን እንዲሰራ ያደረጉት ኢክራም በዚህ የመኪና አካል ማስዋብ ገበያ ላይ ሴቶች በስፋት እንዲገቡ የማድረግ ሥራቸው አልተቋረጠም፡፡

በመስኩ እየተመረቁ ሴቶች መስኩን ከማመላከት ባለፈ በቋሚና በኮንትራት ቅጥር ሰፊ የሥራ ዕድል ፈጥረዋል፡፡ በተጨማሪም ወደ መስኩ የመግባት ፍላጎቱ ላላቸው ስልጠና በመስጠት እንዲሁም የሌላቸው እንዲሰለጥኑ በማድረግ እያገዙ ይገኛሉ። ባለፉት ሦስት ዓመታት ይሄንኑ አዲሱን ሥራቸውን በየድርጅቱ ጭምር እየሄዱ በማስተዋወቅ ነው ያሳለፉት፡፡ በአርቲ ቲቪም እንዲሁ የማስተዋወቅ ሥራውን እየሰራ ይገኛል፡፡ የአዲስ አበባ ንግድና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት (አዲስ ቻምበር) የግሉን ዘርፍ በማጠናከር በሀገሪቱ ንግድና ኢንቨስትመንት ኢንዲስፋፋ የበኩሉን ሚና በመጫወት ላይ እንደሚገኝ የገለፁት የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መሰንበት ሸንቁጤ ‹‹እንዲህ ዓይነት ሴቶች ወደ ላይ እንዲወጡ በየጊዜው ማስታወስ ይፈልጋል›› ባሉት ጽሑፋችንን ደመደምን፡፡

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

ከ55 ዓመት በፊት በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በተለይም እየተጋመሰ በሚገኘው መጋቢት ወር የወጡ ዘገባዎችን ዛሬው ዓምዳችን ለማስታወስ ወደናል። ከመራረጥናቸው ዘገባዎች መካከል አሥር ጥጃ በአገራችን ስለወለደችው ላም፣ ሲጃራ 5 ሳንቲም ጨምረው በ65 ሳንቲም ሲሸጡ የነበሩ ግለሰብ 50 ብር በንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ክትትልና ቁጥጥር ስለመቀጣታቸው ይነግሩናል። እነዚህና ሌሎች ዘገቦችን ዛሬ ላይ መለስ ብለን ስንመለከታቸው ግርምትን የሚፈጥሩ ዘገባዎችን እንደሚከተለው እናስታውስ።

### ላሟ ፲ ጥጃዎች ወለደች

አሰላ፤ (ኢ.ዜ.አ) አንዲት ላም በአንድ ጊዜ አሥር ጥጃዎች ወለደች። ከተወለዱት አሥር ጥጃዎች መካከል አንዱ በተፈጥሮው ትክክለኛ ጥጃ ሲሆን፤ ዘጠኙ ደግሞ መጠናቸው ትንንሽ ነበረ። እነዚሁ መጠናቸው አነስተኛ የሆኑት ጥጆች ወዲያውኑ ሲሞቱ፤ መጠኑ ከነርሱ ከፍ ይል የነበረው 10ኛው ጥጃ ደግሞ ስድስት ቀን ቆይቶ ሞቷል።

የላሚቱ ባለቤት አቶ ወትዩ ድልብቶ የሚባሉት ሲሆኑ፤ በአሩሲ ጠቅላይ ግዛት በጭላ አውራጃ ኮፈሌ ወረዳ ቆሩ ሁዱጋ በሚባለው ቀበሌ የሚኖሩ መሆናቸው ተገልጧል።

**(መጋቢት 15 ቀን 1960 ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን)**

### ስ፳ ሳንቲም ብልጫ ፶ ብር ተቀጡ

**ከአዲስ ዘመን ጋዜጠኛ**

የሐሰት ስም በመስጠትና ‹‹መሐመድ አህመድ ነኝ›› በማለት ሲያስቸግሩ የቆዩት አቶ ደላሞ አብደላ የተባሉ በተሰማ አባቀማው መንገድ ላይ የሚገኙ ነጋዴ ፳ ሳንቲም መሸጥ የሚገባቸውን ሲጃራ አምስት ሳንቲም አስበልጠው በ፳፭ ሳንቲም ስለሸጡ፤ የስድስተኛው ወረዳ ፍርድ ቤት ፶ ብር ቀጥቷቸዋል ሲል የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና ማስታወቂያ ክፍል ገለጠ።

አቶ ደላሞ ፍርድ ቤት ሊቀርቡ የቻሉት፤ ቀደም ብሎ በተሰጠው ተገድደው እንዲቀርቡ በሚለው በዳኛው ትዕዛዝ መሠረት፤ ሐያ አራት ሰዓት ፖሊስ ጣቢያ ገብተው ከታሰሩ በኋላ ነው። ይህም የሆነው፤ ሦስት ጊዜ የፍርድ ቤት ጥሪ ደርሷቸው ባለመቀበላቸውና ሕግን በመጣሳቸው ሲሆን አቶ ደላሞ እስር ቤት እያሉ የንግድ ሱቃቸው ዝግ ነበረ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፍርድ ቤት ቀርበው ዋጋ በማስበለጥ ተከሰው ከተቀጡት ነጋዴዎች መካከል፤ አቶ ደላሞ አስረኛው ናቸው። ተከሳሹ ከንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የተላኩ ተዘዋዋሪ ምድብ የዋጋ ተቆጣጣሪዎች (እንስፔክተር) በከፍተኛ ዋጋ ሲሸጡ እንደያዙዋቸው ተጠይቀው አምነዋል። ፍርድ ቤቱ አሻሽሎ ፶ ብር የቀጣቸውም፤ ወንጀሉን የፈጸሙት በማወቅ ሳይሆን፤ ባለማወቅ በስሕተት መሆኑን አቶ ደላሞ ስላመኑ፤ አስተያየት ተደርጎላቸው መሆኑንም የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና ማስታወቂያ ክፍል በተጨማሪ አብራርቷል።

ከዚህም ጋር በማያያዝ ከዚሁ ክፍል የተሰጠው መግለጫ እንደሚመለከተው፤ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የዋጋ ቁጥጥር ክፍል፤ የከተማውን የዋጋ ሁኔታ በመደበኛና በተወሰነው መሠረት እንዲከበር ለማድረግ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ የማይቆጠብ መሆኑንም ለመረዳት ተችሏል።

**(መጋቢት 17 ቀን 1960 ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን)**

### ዓመፀኛው ዝንጀሮ ተገደለ

አዲስ አበባ፤ (ኢ.ዜ.አ) ሁለት ቀን ሙሉ በመንደር ውስጥ እየተዘዋወረ በሰላማዊ ሰዎች ላይ ጉዳት ያደረሰ ዝንጀሮ ተገደለ። በልደታ ወረዳ መካኒሳ ቀበሌ ውስጥ ከመጣበት ያልታወቀ አንድ ገመር ዝንጀሮ መጋቢት ፲፰ ቀንና መጋቢት ፲፱ ቀን ፯ ሰዎች ነክሶ ከማቁሰሉም በላይ፤ በመንደሩ የሚገኙትን ውሾች ሁሉ እንዲባረሩ አድርጓል።

በዚሁ ዝንጀሮ ከተነከሱት ፯ ሰዎች መካል ፬ቱ በብርቱ ስለቆሰሉ ለሕክምና ወደ ሆስፒታል መወሰዳቸውን ከአሜሪካ ሉተራን ሚሲዮን ቄስ ዓለም ታደሰ በላይ ገልጠዋል። በአውሬው ጉዳት እንዳይደርስባቸው ይከላከሉ ከነበሩት ሠፈርተኞች መካከል የስካንስካ ጋራዥ ሠራተኞች ትናንት በ፲፩ ሰዓት ገደማ ላይ በሦስት ጥይት ከመቱት በኋላ፤ ዝንጀሮው የሞተ መሆኑን ከሠፈርተኛው ለመረዳት ተችሏል። ዝንጀሮው ጤነኛ ወይም በውሻ በሽታ የተለከፈ መሆን አለመሆኑ የመካኒሳ ቀበሌ ምክትል ፖሊስ ጣቢያ ሊያረጋግጥ አልቻለም። በሠፈርተኛው ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰው ዝንጀሮ እሬሳ አሁንም ከመካኒሳ በታች ከሚገኘው ወንዝ ዳር ተጥሎ ይገኛል።

**(መጋቢት 21 ቀን 1960 ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን)**

### የመንግሥት ሹማምንት ሚስት ማግባት አለባቸው

ከናይሮቢ፤(ሮይተር) ‹‹ የሌላውን ሰው ችግር ለመገንዘብ እንደችሉ፤ መሪዎች ሆኑ ሁሉ ሚስቶች ስለሚያስፈልጓቸው፤ የኬንያ ካቢኔ ሚኒስትሮች፤ ሌሎችም ከፍተኛ ሹማምንትና የምክር ቤት አባሎች ሚስቶች ማግባት አለባቸው ሲሉ አንድ የኬንያ ምክር ቤት እንደራሴ ከትናንት ወዲያ ሀሳብ አቀረቡ።

የኬንያ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ ሚስተር ቻርልስ ንጆንጆ ትዳር መያዝ የማስፈለጉን ጉዳይ እንዲገነዘቡት በሀሳብ አቅራቢው ተጠይቀው እንደነበር ታውቋል።

አርባ ዘመናቸውን ያለ ሚስት ያገባደዱት ሚስተር ንጆንጆ ግን ‹‹ ይህ የግል ጉዳይ ነው። ›› ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል። ጠቅላይ ዓቃቤ ሕጉ ንግግራቸውን በፈገግታ እያሳመሩ በሰጡት ምላሽ ለማግባት ሀሳብ ኖሮኝ ምኞቴን በገቢር ለመግለጽ ብዙ ሴቶች ጠይቄ እንቢም ብለውኝ ለብቻ መኖሬን ለምክር ቤቱ ለመግለጥ የማልፈልገው ነበር ›› አሉ።

**(መጋቢት 17 ቀን 1960 ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን)**

# ዓለም አቀፍ

## በደቡብ አፍሪካ የሙስና ወንጀሉች መርማሪው ከነልጃቸው ተገደሉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በደቡብ አፍሪካ ከፍተኛ የሙስና ወንጀሎችን የሚመረምሩት ግለሰብ በተከፈተባቸው ተኩስ ከልጃቸው ጋር ተገደሉ።

ክሎቴ ሙሬይ የተባሉት የ50 ዓመቱ መርማሪ ቧሳሳ ከተባለው እና ከመንግሥት ጋር በገባቸው በርካታ የቅሌት ውሎች የሚታወቀውን ድርጅት መርምረዋል።

በተጨማሪም ምንም እንኳን ኩባንያው ክሱን ባይቀበልም ጉቦ በመስጠት የተጠረጠረ አንድ ትልቅ ኩባንያ ላይ ምርመራ አድርገዋል።

በሟቹ መርማሪና ሲመረምሯቸው በነበሩት ጉዳዮች መካከል ግንኙነት መኖሩን ወይም አለመኖሩን ፖሊስ ይመለከተዋል ተብሏል።

መርማሪው ባለፈው ቅዳሜ የሕግ አማካሪ ከሆነው የ28 ዓመት ልጃቸው ቶማስ ጋር መኪናቸውን እየሸከረከሩ ሳለ ማንነቱ ባልታወቀ ሰው ተተኩሶባቸው ተገድለዋል።

ልጃቸው ወዲያው እንደሞተ እና እሳቸው ግን ሆስፒታል ከገቡ በኋላ ሕይወታቸው ማለፉን የደቡብ አፍሪካ መገናኛ ብዙኃን የፖሊስ ቃል አቀባዩን ጠቅሰው ዘግበዋል።

አባት እና ልጅ ፕሪቶሪያ ወደሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው እያቀኑ ሳለ መገደላቸውን መገናኛ ብዙኃኑ ዘግበዋል።

ሙሬይ በፍርድ ቤት የተዘጉ ኩባንያዎችን እንዲመረምሩ፣ ንብረቶችን እንዲያስመልሱ እና ወንጀሎችን ሪፖርት እንዲያደርጉ ተሹመው ነበር።

ከእነዚህ ድርጅቶች መካከል አንዱ ቧሳሳ ነው። ቧሳሳ በተለይም በእስር ቤቶች አገልግሎት ላይ የተሰማራ ሲሆን ከመንግሥት ጋር ውል የሚገባ ነው።

ታዋቂው ዞንዶ የተባለው የፀረ ሙስና ኮሚሽን ቧሳሳ እንደ አውሮፓውያኑ ከ2009 እስከ 2018 በነበረው የጃኮብ ዙማ የሥልጣን ዘመን ለመንግሥት ባለሥልጣናትን እና ፖለቲከኞች ጉቦ ይሰጥ እንደነበር ደምድሟል። ዙማ ለምርመራው አልተባበርም ቢሉም የሙስናውን ክስ አይቀበሉትም።

እንደ አውሮፓውያኑ በ2018 የአሁኑ ፕሬዚዳንት ሲሪል ራማፎሳ ከቧሳሳ የተቀበሉትን 35 ሺህ ዶላር መልሰው እንደሚከፍሉ መግለጻቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

ራማፎሳ የገንዘብ ስጦታውን በተመለከተ ፓርላማውን እንዳሳሳቱት የፀረ ሙስና ኮሚሽኑ ቢደርስበትም ጉዳዩ በፍርድ ቤት ውድቅ ተደርጓል።

ራማፎሳ ባይቀበሉትም በሌላም ሙስና እንደተሳተፉ




ተወርቶባቸዋል። ሟቹ መርማሪ ጉፕታ ብራዘርስ የተባለው ድርጅትንም የሙስና ጉዳዮችን ሲመረምሩ ነበር።

ዞንዶ ኮሚሽን ኩባንያው በዙማ የሥልጣን ዘመን የመንግሥትን ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ውሳኔዎች ላይ ጫና ለማሳደር ሞክሯል ብሏል።

ጉፕታ ብራዘርስ እንደ አውሮፓውያኑ በ1993 ከሕንድ ወደ ደቡብ አፍሪካ የተዘዋወረ ሲሆን፣ ከመንግሥት ኩባንያዎች ጋር ከፍተኛ ትርፍ የሚያስገኙ ውሎችን በመፈረም የሚታወቅ ነው።

የደቡብ አፍሪካ ባለሥልጣናት በዩናይትድ አረብ ኤምሬትስ የታሰሩት ጉፕታ ብራዘርስ ወደ ደቡብ ተዘዋውረው ለፍርድ እንዲቀርቡ እየሰሩ ነው። ኩባንያው የመንግሥትን ውል ለማግኘት ጉቦ ይሰጣል መባሉን ግን አስተባብሏል።

## የአፍጋኒስታን ባለሥልጣናት ለመንግሥት ሥራ የቀጠሯቸውን ዘመዶቻቸውን እንዲያሰናብቱ ታዘዙ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በአፍጋኒስታን የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ዘመዶቻቸውን የቀጠሩ ባለሥልጣናት ከሥራ እንዲያሰናብቱ ታሊባን አዘዘ።

የመንግሥት ባለሥልጣናት የቀጠሯቸውን ልጆቻቸውን እና ዘመዶቻቸውን በማሰናበት በምትኩ በሌሎች እንዲተኩ እንዲሁም ወደፊት ከዚህ ዓይነት ተግባር እንዲቆጠቡ ታሊባን አሳስቧል።

እንደ አውሮፓውያኑ በ2021 ታሊባን ወደ ሥልጣን ሲመለስ ልምድ ያላቸውን ሠራተኞች ያባረረ ሲሆን፣ ሌሎች ደግሞ አገሪቱን ጥለው ተሰደዋል።

በዚህም ምክንያት ከባለሥልጣናት ጋር ባላቸው ግንኙነት ምክንያት ልምድ የሌላቸው ሠራተኞች በመንግሥት ተቋማት ውስጥ ተቀጥረዋል የሚሉ መረጃዎች ተናፍሰዋል።

መቀመጫውን በፓኪስታን ፔሻዋር ያደረገው አፍጋኒስታን ኢስላሚክ ፕሬስ እንደዘገበው ከሆነ የአፍጋኒስታን ባለሥልጣናት ልጆቻቸውን በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች በመሾማቸው ታሊባን



ይህንን ለማስተካከል ትዕዛዝ አውጥቷል።

ባለሥልጣናቱ የታዘዙበት ይህ ማስታወቂያ ፎቶ በአስተዳደራዊ ጉዳዮች ቢሮ የትዊተር ገጽ ላይ ተለጥፎ ታይቷል።

ታሊባን መልሶ ሥልጣን ከተቆጣጠረ በኋላ የከፋ የኢኮኖሚያዊ እና የሰብአዊ ቀውስን እየተጋፈጠ ነው።

በአገሪቱ የውጭ ኃይሎች ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ የቆዩ ሲሆን፣ በ10 ሺህ ሚቆጠሩ ሰዎች እንዲሞቱ እና በሚሊዮኖች እንዲፈናቀሉ ምክንያት የሆነ ጦርነት ሲያካሂዱ ቆይተዋል።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በታሊባን መንግሥት ባለሥልጣናት ላይ ማዕቀብ የተጣለ ሲሆን፣ ባሕር ማዶ የሚገኙ የአገሪቱ ማዕከላዊ ባንክ ንብረት ታግዷል።

በተጨማሪም በውጭ አገራት የሚገኙ በርካታ የአፍጋኒስታን ንብረቶች የታገዱ ሲሆን፣ ይህም የአገሪቱን ኢኮኖሚ አሽመድምዷል።

አፍጋኒስታን 1 ትሪሊዮን ዶላር የሚገመት የተፈጥሮ ጋዝ እና መዳብን ጨምሮ በርካታ የተፈጥሮ ሃብት እንዳላት ይገመታል። ሆኖም ይህ ሃብት ለአስርት ዓመታት በዘለቀው አለመረጋጋት ምክንያት ጥቅም ላይ መዋል አልቻለም።

የታሊባን መንግሥት በሴቶች ላይ ያለው አሉታዊ አያያዝ እና አመለካከት በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲነቀፍ እና የአገሪቱ ኢኮኖሚ እየተዳከመ ባለበት ጊዜ ከዓለምአቀፉ ሕብረተሰብ እየተነጠለ እንዲሄድ አድርጎታል።

በአሁኑ ወቅት ሴቶች በአብዛኛው አፍጋኒስታን ውስጥ ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እና ከዩኒቨርሲቲዎች ታግደዋል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጻችንንና ፌስቡክ ገጻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ማክሰኞ ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

## ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በድል የደመቁባቸው የጎዳና ላይ ውድድሮች

**ብርሃን ፈይሳ**

የሳምንቱ መጨረሻ ቀናት እንደተለመደው በበርካታ የዓለም ከተሞች የጎዳና ላይ ውድድሮች በብዛት የተካሄዱበት ነው። በርካታ ኢትዮጵያውያን አትሌቶችም በነዚህ ውድድሮች የተለመደ ድልና ውጤታማነት አልተለያቸውም።

በተለያዩ ከተሞች ከተካሄዱ ውድድሮች መካከል በደቡብ ኮሪያዋ ሴኡል የተከናወነው ማራቶን በቀዳሚነት ይጠቀሳል። በዓለም አትሌቲክስ የፕላቲኒየም ደረጃ በተሰጠው በዚህ የማራቶን ውድድር በወንዶች ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ከአንድ እስከ አምስት ያለውን ደረጃ በመያዝ በፍፁም የበላይነት አጠናቀዋል።


በውድድሩ ቀዳሚ ሆኖ ያጠናቀቀው ኢትዮጵያዊ አትሌት አምደወርቅ ዋለልኝ ሲሆን በርቀቱ የግሉን ፈጣን ሰዓት ማስመዝገብ ጭምር ማሸነፍ ችሏል።

አትሌት አምደወርቅ ከወራት በፊት በዚሁ ከተማ በተካሄደ የማራቶን ውድድር ላይ ተሳትፎ ፉክክሩን ያጠናቀቀው በአሸናፊነት ነበር። በወቅቱ የገባበት ሰዓትም 2:06:59 ቢሆንም፤ ከትላንት በስቲያ በነበረው ውድድር አንድ ደቂቃ በማሻሻል 2:05:27 በሆነ ሰዓት ርቀቱን በቀዳሚነት ማጠናቀቅ ችሏል።

እአአ የ2020 የዓለም ግማሽ ማራቶን የነሃስ ሜዳሊያ አሸናፊ የነበረው አትሌት አምደወርቅ የአገሩን ልጆች አስከትሎ በቀዳሚነት ያጠናቀቀው በጥቂት ሰከንዶች ልዩነት ሲሆን ይህም ውድድሩን በጠንካራ ፉክክር የታጀበና አጓጊ አድርጎታል። ኢትዮጵያውያኑ አትሌቶች ሽፈራ ታምሩ እና ሃፍቱ ተክሉ በሰከንዶች ልዩነት ሁለተኛ እና ሶስተኛ ደረጃን ይዘው ባጠናቀቁበት በዚህ ውድድር፤ አሊቃ አዱኛ እና አሸናፊ ሞገስ በአንድ ደቂቃ ልዩነት አራተኛ እና አምስተኛ ደረጃን በመያዝ ጠንካራ ፉክክር አድርገው ውድድራቸውን ማጠናቀቅ ችለዋል።

በፈረንሳይ ሊል ከተማ በተካሄደ ሌላ የጎዳና ላይ የሩጫ ውድድርም በተመሳሳይ ኢትዮጵያዊ አትሌት አሸናፊ ሊሆን ችሏል። በ5 ኪሎ ሜትር በተካሄደው ውድድር አትሌት ዮሚፍ ቀጄልቻ ቀዳሚ ሆኖ ያጠናቀቀ አትሌት ሲሆን የርቀቱን የዓለም ክብረወሰን ለመስበር ያደረገው ጥረት ሊሳካለት አልቻለም። የሁለት ጊዜ የዓለም የቤት ውስጥ ቻምፒዮኑ አትሌት ዮሚፍ በአገሩ ልጅ አትሌት በሪሁ አረጋዊ ተይዞ የቆየው የርቀቱን ክብረወሰን (12:49) ለማሻሻል ያደረገው ጥረት በአንድ ሰከንድ በመዘግየቱ ከእጁ ሊወጣ ችሏል። አትሌቱ የገባበት 12:50 የሆነ ሰዓትም በርቀቱ የግሉ እንዲሁም የርቀቱ ሁለተኛው ፈጣን ሰዓት ሆኖ ሊመዘገብ ችሏል። ዮሚፍን ተከትሎ ኬንያዊው ሪኖልድ ኪፕኮሪር ሁለተኛ ሆኖ ሲያጠናቅቅ፤ አትሌት ጥላሁን ኃይሌ ደግሞ ሶስተኛ ሆኖ ውድድሩ የፈጸመ ኢትዮጵያዊ አትሌት ሆኗል። በተመሳሳይ በሴቶች መካከል በተካሄደው ውድድር አትሌት መቅደስ አበበ በሁለት ኬንያውያን መካከል በመግባት ሁለተኛ ሆና ውድድሯን ፈጽማለች።

ሌላው ትልቅ ትኩረት በተሰጠው በኒውዮርክ ግማሽ ማራቶን ውድድር የሁለት ጊዜ የ5ሺ ሜትር የዓለም ቻምፒዮኗ ኬንያዊት አትሌት ሄለን ኦቤሪ አሸንፋለች።



**ኢትዮጵያዊው አትሌት አምደወርቅ ዋለልኝ በሲውል ማራቶን የግሉን ፈጣን ሰዓት አስመዝግቦ አሸንፏል፤**

ከኦቢሪ ጋር ብርቱ ፉክክር ያደረገችው ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ሰንበሬ ተፈሪ በበኩሏ በ34 ሰከንዶች ብቻ ተቀድማ ሁለተኛ ደረጃን በመያዝ ውድድሩን ጨርሳለች። ከውድድሩ የመነሻ አንስቶ ከፍተኛ ትንቅንቅ ሲያደርጉ የቆዩት ሁለቱ አትሌቶች በሰከንዶች ልዩነት ብቻ ተከታትለው ለመግባት ያደረጉት አስደናቂ ፉክክር የብዙዎችን ቀልብ የገዛ ነበር። በዚህም ኢትዮጵያዊቷ አትሌት ሰንበሬ የገባችበት ሰዓት 1:07:55 ሆኖ ተመዝግቦላታል።

ሌላኛው ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በስፋት የተካፈሉበትና ለውድድሩም ድምቀት የነበሩበት ውድድር የሮም ማራቶን ሲሆን፤ በወንዶች መካከል በተካሄደው ውድድር ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ከፍተኛ የአሸናፊነት ግምት ቢሰጣቸውም ቀዳሚውን ውጤት ማስመዝገብ ሳይችሉ ቀርተዋል። አበበ ቢቂላ ከ63 ዓመታት በፊት በዚህችው ታሪካዊ ከተማ በባዶ እግሩ ያስመዘገበው የኦሊምፒክ ማራቶን ድል የተዘከረበት መንገድ የብዙዎችን ትኩረት አግኝቶ ውሏል። የቀድሞ የታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ ስራ አስኪያጅ የነበረው ኤርሚያስ አየለ የጀግናውን አትሌት አበበ ቢቂላ የሮም ኦሊምፒክ ገድል ለማስታወስ፤ 42 ኪሎ ሜትሩን ቃል በገባው መሰረት በባዶ እግሩ በመሮጥ አጠናቋል። ይህም በውድድሩ ተሳታፊ ከነበሩ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ይልቅ የበርካታ መገናኛ ብዙሃንን ትኩረት ያገኘ ሆኗል። በአንጻሩ በሴቶች መካከል በተካሄደው ውድድር ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ቀዳሚ ሆነው ማጠናቀቅ ባይችሉም በአትሌት ፎዚያ አሚድ እና ዝናሽ ደበበ አማካኝነት የሁለተኛና ሶስተኛ ደረጃ ውጤት ሊመዘገብ ችሏል።

ከሮም ማራቶን ይልቅ በአንፃራዊነት ብዙ ግምት ባልተሰጠው በሎሳንጀለስ ማራቶን በወንዶች ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ተከታትለው በመግባት አሸናፊነታቸውን አረጋግጠዋል። ርቀቱን በቀዳሚነት የፈጸመው አትሌት ጀማል ይመር ሲሆን፤ የገባበት ሰዓትም 2 ሰዓት ከ13 ደቂቃ ከ14 ሰከንድ ሆኖ ተመዝግቧል። አትሌት የማነ ጸጋዬ ደግሞ በአንድ ደቂቃ ዘግይቶ ሁለተኛ ደረጃን ይዞ የፈፀመ ኢትዮጵያዊ አትሌት ነው።

Ethiopian Cooperative Commission (ECC)
የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን

ከኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር
በየሳምንቱ የሚታተም

## በተለየ ጣዕማቸው ተፈላጊነት ያላቸው የመተከል ዞን የዱባ ዝርያዎች

**በአስምነህ ቸርነት**

የዱባ ምርት በዓለማችን በአብዛኛው ክፍሎች የሚመረት ነው። ኢትዮጵያ ለዱባ ምርት ምቹና ተስማሚ የአየር ንብረት አላት። በኢትዮጵያ ዱባ በአብዛኛው በቆላማ አካባቢዎች የሚመረት ሲሆን ከእነዚህ መካከል መተከል ዞን አንዱ ነው። የዱባ ተክል የሚሰጠው ምርት በአፈሩ አይነት፣ በተክሉ እድሜ፣ በምርት አተገባበርና አያያዝ ይወሰናል።

ዱባ ከፍተኛ ምርታማነት ያለው፣ ሳይበላሽ ለረጅም ጊዜ መቆየት የሚችልና ከፍተኛ የምግብ ንጥረ ነገር የያዘ ተክል ነው። ዱባ ለጤና አስፈላጊ የሆኑ እንደ ፕሮቲን፣ ካርቦ ሃይድሬትና ሚኒራሎች ባሉ ንጥረ ነገሮች የበለጸገ ነው። የዱባ ምርት ለምግብነት ከመዋሉ ባለፈ የስኳር በሽታ፣ የኩላሊት ጠጠር፣ የደም መርጋት የመሳሰሉ የጤና ችግሮችን ለመከላከል ጉልህ ጠቀሜታ አለው። ሆኖም ግን በአገራችን ስለ ምርቱ ሁኔታና በስነምግብ ረገድ ስለሚሰጠው ጠቀሜታ በህብረተሰቡ ዘንድ ያለው መረጃና ዕውቀት ውስን በመሆኑ ምርቱን በስፋት አይጠቀምበትም።

ዱባ በመተከል ዞን በሰባቱም ወረዳዎች ይመረታል። የአካባቢው ዱባ ክረምት መግቢያ ላይ ከሰኔ ወር ጀምሮ ተዘርቶ ከመስከረም እስከ ታህሳስ ባሉት ወራት ምርት ተሰብስቦ ለገበያ ይቀርበል። የጉሙዝ ማህበረሰብ ዱባን በቋንጣ፣ በወጥና በጥብስ መልክ ሰርቶ ለምግብ ፍጆታ ይጠቀመዋል። በምርቱ ላይ እሴት በመጨመር



ዱባን አድርቆና ፈጭቶ እንደ ሽሮ መጠቀምም ይቻላል።

የዱባ ምርት እንደ ሀረግ የሚያድግ ተክል በመሆኑ እራሱን በቻለ መሬት የሚመረት ሳይሆን ከሌላ ሰብል ጋር በአብዛኛው ከበቆሎ ጋር ይመረታል። አርሶ አደሩ ዱባን የሚያመርተው ምንም አይነት ሰው ሰራሽ ማዳበሪያ ወይም ምርጥ ዘር ሳይጠቀም ነው።

ምርቱ እንደ ሌሎች ሰብሎች በኤክስቴንሽን ታቅፎ በሳይንሳዊ ዘዴ የሚመረት አይደለም። በዞኑ በአሁኑ ግዜ እስከ 439 ሄክታር የሚሸፍን የዱባ ምርት እየተመረተ ይገኛል። በአካባቢው አሁን ባለው ሁኔታ የዱባ ምርትን ከአንድ ሄክታር እስከ 250 ኩንታል ማግኘት ይቻላል።

በመተከል ዞን በጣም ብዙ አይነት የዱባ ዝርያዎች እንደሚገኙ በፓዊ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት አማካይነት ጥናት ተደርጓል። በዚህም መሰረት ወደ 49 የሚሆኑ አገር በቀል የዱባ ዘረ መል ተሰብስቦ ከእነዚህ ውስጥ በጣዕማቸው የተሻሉ የተባሉት ወደ ዘጠኝ የሚሆኑት በአካባቢያቸው ተለይተው ተመርጠዋል። በአሁኑ ጊዜ ዘረመሎቹን አባዝቶ ማቅረብ ባይቻልም በመረጃ ደረጃ መስፈርት ወጥቶላቸው ተቀምጠዋል። እነዚህም የድባጤ ዱባ፣ የቡለን ዱባ፣ የዳንጉር ዱባ፣ የመንታውሃ ዱባ፣ የማንኩሽ ዱባ፣ የማንዱራ ዱባ፣ የፓዊ ዱባ፣ የጉባ ዱባና የጃዊ ዱባ የሚባሉ ናቸው።

በመተከል ዞን የሚገኙት የዱባ ዝርያዎች በቅርጽ፣ በቀለም፣ በመጠን፣ በቅጠል፣ በፍሬና በክብደት የሚለያዩ ሲሆን ከክብደት አንጻር በአማካይ ከአምስት እስከ አስር ኪሎ ግራም ይመዝናል። እንዲሁም አንዳንዴ እስከ 19 ኪሎ ግራም ክብደት ያለው የዱባ ዝርያ ይገኛል። የጣፋጭ ዱባ ቅርጹ ሞላላ ሆኖ ብዙ የመስመር ክፋዮች ያለው ነው። ቀለሙ የቢጫና ቀይ ቅልቅል (ሳምባ) የመሰለ ነው። ምርቱ እስከ አንድ ዓመት ድረስ የቆይታ ግዜ ሊኖረው የሚችል በመሆኑ አርሶ አደሩ ምርቱን ከሰበሰበ በኋላም ቢሆን ለረጅም ግዜ በቤቱ ውስጥ አስቀምጦ ሊጠቀምበት ይችላል።

የአካባቢው አርሶ አደር ምርቱን በራሱ መሬት እያመረተ ለራሱ ፍጆታ ከመጠቀም ውጪ የተረፈውን በችርቻሮ መልክ በአካባቢው ገበያ ለተጠቃሚዎች እያቀረበ ነው። ሆኖም ግን ለማዕከላዊ ገበያ ማቅረብ እንደሚቻል ማህበረሰቡ ከተረዳ ከዚህ የበለጠ ማምረት የሚቻልበት ዕምቅ አቅም እንዳለ ለማየት ይቻላል። በአሁኑ ጊዜ አርሶ አደሩ ትልቅ የሚባለውን ዱባ ሳይመዝን በግምት ከብር 150 እስከ ብር 200 ይሸጣል። አነስተኛውን ደግሞ በብር 50 ይሸጣል። ዱባ የሚሸጠው በሚዛን ሳይሆን በግምት ነው። የመተከል ዱባ አልፎ አልፎ ወደ ሌላ ቦታ እየተወሰደ በብር 200 የተገዛው እስከ ብር 500 ይሸጣል።

በዞኑ ኅብረት ሥራ ማህበራት ቢኖሩም ከዱባ ጋር ተያይዞ የሚሰሩት ስራ የለም። ሆኖም ግን የዱባ ምርታማነትን በማሳደግ የግብይት ትስስር የሚፈጠርላቸው ከሆነ ምርቱን በማልማትና በግብይት ውስጥ ገብተው መስራት የሚችሉበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። ስለሆነም ተፈላጊነት ያለው የዱባ ዝርያ ላይ የብራንዲንግ ፕሮሞሽን ስራ በመስራት አንድም ምርቱ በማህበረሰቡና ተጠቃሚው ዘንድ እንዲታወቅ ማድረግና አርሶ አደሩም የተሻለ አምርቶ ከሰብሉ እንዲጠቀም ማስቻል ያስፈልጋል።

በአጠቃላይ በመተከል ዞን በዱባ ምርትና ምርታማነት ላይ በትኩረት እየተሰራ ባለመሆኑ ምርታማነቱ እየቀነሰ የመጣበት ሁኔታ ይታያል። በምርምር ተለይተው በታወቁ የዱባ ዝርያዎች ላይ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግና የገበያ ተደራሽነቱን ለማስፋት የዞኑና ወረዳዎች የግብርናና ኅብረት ስራ ጽ/ቤት፣ የፓዊ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩትና በዞኑ የሚገኙ መንግስታዊ ያልሆኑ ባለድርሻ አካላት በተቀናጀ አግባብ መስራት ይጠበቅባቸዋል።

አድራሻ | የፌዴራል ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | 0115573448/ 0118592105 | ፖ.ሳ.ቁ. 19787 | Facebook: Federal cooperative Agency | Website: www.fca.gov.et